# *የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች ትንተና በመንግሰቱ ለማ ፀረ ኰሎኒያሊስት ተውኔት*

**አብዮት ዓለም [1]፣ አየነው ጓዱ** [2]

## አሕጽሮተ ጥናት

*ይህ ጥናት "የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች ትንተና በመንግስቱ ለማ ፀረ ኮሎኒያሊስት ተውኔት" በሚል ርዕስ የተከናወነ ነው። በጥናቱ ከተጠኘ ተውኔቱ የተቀነጨቡ ሃሳቦችን በማቅረብ የንድፈ ሃሳባዊ ዳራውን ገቢራዊነት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በጥናቱ ተውኔቱን በምን መሥፈርት እንደተመረጠ፣ በምን ዘዴ እንደተነተኑ፣ የመረጃ ምንጮችንና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እንዲሁም የመረጃ አተናተን ስልትና ሂደት ቀርቧል። ጥናቱን ለመተንተን የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። በጥናቴም በተውኔቱ ውስጥ የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ መገለጫ ጭብጦች በምን መልኩ እንደተከሰቱ አሳይቷል። ይህ ጥናት ከተውኔቱ ውስጥ ተቀንጭበው በሚቀርቡ ማሳያዎች ላይ በመመስረት ከአውሮፓ ማዕካላዊነት (eurocentirism)፣ከምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (orientalism)፣ ከባይተዋርነት (unhomeliness)፣ ከራስን አለመሆን (Mimicry)፣ ከገዥ-ተገዥ ድልድል (Hegemony) እና ቋንቋ፦ድምፅ አልባው ጠመንጃ ከሚሉት ጭብጦች አንፃር ትንታኔ በመስጠት የድህረ ቅኝ ግዛት የሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ መገለጫዎችን አሳይቷል። በአጠቃላይ ፀረ ኰሎኒያሊስት የተሰኘው ተውኔት የድህረ ቅኝ ግዛት የሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ መገለጫዎችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ችለናል።*

***ቁለፍ ቃላት፦*** *የድህረ ቅኝ ግዛት ሂስ፣የአውሮፓ ማዕከላዊነት፣የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ፣የገዥ-ተገዥ ድልድል*

## *መግቢያ*

ጸሐፌ ተውኔት መንግሥቱ ለማ *የተውኔት ጉባኤ* (1975) በሚለ ያሳተመው መድብል ሁለት ተውኔቶች ያያዘ ሲሆን፣ እነሱም *ፀረ ኮሎኒያሊስት* (1975a) እና *ባለካባና ባለዳባ (1975b)* የተሰኙ ናቸው። ለዘህ ጥናት የተመረጠው *ፀረ ኰሎኒያሊስት* (1975a) የተሰኘው ተውኔታቸው በቀጥታ በሁለተኛው የጣልያን ወረራ ላይ ተመሥርቶ የተጻፈና የአርበኞችን እና የውስጥ አርበኞችን ትግል የሚያሳይና ህዝቡን ለአካል ብቻ ሳይሆን ለአዕምሮ ቅኝ ግዛት እጁን እንዳይሰጥ የሚያነሳሳ ነው። ከዚህም ባሻገር ቅኝ ለመግዛት የመጣውን ጣልያንን የሥልጣኔና የዘመናዊነት አርዓያ እና ማዕከል አድርጎ (eurocenterism) ህዝቡ እንዲቀበልና እንዲከተለው በሚያደርጉና ይህንን አስተሳሰብ በግልፅም በህቡዕም በመቃወም ሕዝቡን በጣልያን ላይ በሚያነሳሱ መካከል የሚደረግ ትግልን የያዘ ተውኔታዊ ታሪክ ነው።

*ይህ ጥናተ የድህረ ቅኝ ግዛት የሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብን በመተንተኛ ዘዴነት ተጠቅሟል።* የዚህ ንድፈሃሳብ ቁልፍ አራማጆች፣ በተለይም Frantz Fanon (1952፣1961)፣ Edward Said (1978)፣ Homi Bhabha (1990፣1994)፣ Harrison (2003) እና Gayatri Spivak

[1] ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ፣ ባሕር ዳር፤ኢትዮጵያ
*Corresponding email:* abiyotalem7@gmail.com

[2] ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ እንግሊዝኛ ት/ት ክፍል፤ ባሕር ዳር፤ኢትዮጵያ

(1988) በሚያነሷቸው ጽንሰሃሳቦች ላይ በመመስረት የተመረጠውን ተውኔት ለማንበብና ለመተንተን ተሞክሯል።

ኬንያዊው እውቅ የሥነጽሑፍ ሰው Ngugi wa Thiong'o (1994) ካስተዋወቃቸው ጽንሰሃሳቦች አንዱ "የአዕምሮ ነፃነት ትግል..." ("Decolonizing the Mind") በያዘው ሃሳብ መሠረት የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ወደ ማንነቱ ሊመለስ እንደሚገባው ወይም ደግሞ አውሮፓ አውሮፓ ከመሸተት ነፃ ሊወጣ የሚገባው ጉዳይ ነው። የአዕምሮ ነፃነት ትግል በተለይም ከቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ጋር ይቆራኛል። Ashcroft et al (2004, p. 56) እንዳሰፈሩት "decolonizing the mind" የሚለው ጽንሰሃሳብ አንድን የቅኝ ተገዥነት አስተሳሰብና የሥነልቦና ባርነት ፍቆ ለማስወጣትና ወደነባሩ ማንነት ለመመለስ የሚደረግን ትግል ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። በተለይም ድብቅ በሆነ ስልት በአዕምሮ ውስጥ ተቀርፆ እንዲቀርና በኋላም በእሱ ተፅዕኖ ውስጥ የሚጥልን የህሊና ባርነት የማፍረስና ነፃነትን የማጎናፀፍ ሂደት እንደሆነም አስፍረዋል።

አዕምሮን ነፃ የማውጣት ትግል በጦር መሣሪያ ቅኝ ገዡን ተዋግቶ እንደማባረር አይደለም፤ በጦር ጀግንነት የተባረሩት ቅኝ ገዥዎች ባህል፣ አስተሳሰብ፣ ሥነውበት እና ሌሎች ረቂቅ ሃሳቦች በማንነት ላይ ያሳደሩትን ተፅዕኖና ውርስ ማፍረስ ነው። እንግዲህ የአዕምሮ ነፃነት ትግል አዕምሮንና አስተሳሰብን በአውሮፓና አሜሪካ ማዕከልነት ከማስገዛት ማስፈታት እንደሆነም እንረዳለን። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ አውሮፓንና አሜሪካን ማዕከል አድርገው በተበጁት የትምህርት ሥርዓቶችና ተቋማት የሚገለፁ በመሆኑ የአዕምሮ ነፃነት ትግሉ በአጭር ጊዜ ሊጠናቀቅ የማይችል መሆኑን Ngugi (1994, p. 6) ካሰፈረው ሃሳብ መረዳት እንችላለን።

በቅኝ ግዛትና በድህረ ቅኝ ግዛት ዘመን በቅኝ በተያዙትና በአካል ባይሆንም በተለያየ ስልት አውሮፓንና አሜሪካን ማዕከል (eurocenterism) አድርገው እነዲሥሉና እንዲቀበሉ የተደረጉ ሀገራት የፖለቲካ ቅኝ አገዛዙ ከተወገደ በኋላም የቅኝ ገዥዎቹ ሥነ ልቦናና አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ቋንቋ ተፅዕኖው መቀጠሉ በሥነ ጽሑፋቸው ላይ ጎልቶ ይታያል (Ashcroft, et al. 1995; Tyson, 2006; Dobie, 2012)። ጣልያንም ኢትዮጵያን በአካል በቅኝ ግዛት ሥር ለማዋል ያደረገችው ሙከራ በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመን በ1888 ዓ.ም አድዋ ላይ ድል ተደርጋ ብትመለስም፤ በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በ1928 ዓ.ም ዳግም ቅኝ ለማድረግ ያደረገችው ሙከራም በአርበኞቿ ተጋድሎ የአካል ቅኝ ገዥነቷ በአጭር ቢቀጭም፣ የቅኝ ተገዥነት አስተሳሳብን ራዕዩን የማሳካት ዓላማው ግን በሥውር እንዲሰርፅ ተደርጓል (Bahru፣ 2002፣ Regassa፣ 1980)።

ይህ በአካል ቅኝ ሳይገዙ የቅኝ ተገዥነት አስተሳሰብ እንዲሰርፅ ደግሞ ሀገሪቱን በማዘመን ሰበበ ዜጎቿን አውሮፓና አሜሪካ ወስዶ ማስተማርና የተለያዩ ዓለማቀፍ ሥራዎችን ማመቻቸት ትልቅ ሥፍራ ነበራቸው። ይህ ተግባርም በአካል ቅኝ ያልተገዛው የድህረ ቅኝ ግዛት አስተሳሳብ ሰለባ ለሆነው አውሮፓን የሁሉም ነገር ማዕከልና ማጠንጠኛ እንዲሁም የሙያዎች ሁሉ ማጣቀሻ የማድረግ ወጥመድ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል። ይህ አስተሳሰብ በተለይ ከሁለተኛው የጣልያን ወረራ በኋላ ጎልቶ የወጣ ነው ማለት ይቻላል። አስተሳሰቡም ከሚገለፅባቸው አንዱ የሥነጽሑፉ ዘርፍ ነው። ለጥናት የመረጥሁት የመንግሥቱ ለማ *ፀረ ኮሎኒያሊስት* (1975a) በተሰኘ ተውኔት አውሮፓን አድራጊ ፈጣሪና የሁሉ ነገር ማዕከል አድርገው በተቀበሉትና ይህንን በሚቃዎሙትና የአስተሳሰብን ቅኝ ተገዥነት ለማፍረስ የሚታገሉ በመኖራቸው የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍን በዓይናቸው የሚጠቅሱ ናቸው። ይህ መሥመር ደግሞ በጥናቴ "የአዕምሮ ነፃነት ትግል" ይደረግበታል ወዳልሁት የድህረ ቅኝ ግዛት ንድፈ ሃሳብ ያደርሰኛል።

የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነጽሑፍ ንድፈሃሳብ በጉልህ መውጣት የጀመረው በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ ሀገራት ለነፃነት መታገል ሲጀምሩ እና ከፖለቲካ አገዛዝ ነፃ ከወጡ በኋላ በመጣው አስተሳሰብ ነው። በተለይም በአፍሪካ፣ በእስያ እና በደቡብ አሜሪካ በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ ሀገራት ነፃነታቸውን ለማስመለስ ትግል ሲጀምሩና ነፃ ከወጡ በኋላ የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነጽሑፍ ሒስ ንድፈ ሃሳብ ሥር መያዙ ይገለፃል (Habib, 2005, p. 738)።

ብሪታንያ በዓለም ላይ ሰፊ ቅኝ ግዛት የነበራት ሀገር ናት፤ በተለይም እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ይህ ይዞታዋ ተጠናክሮ የዓለም ጠቅላይነቷን አስጠብቃ መቀጠል ችላ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ የነፃነት ትግል ሲጀመር የድህረ ቅኝ ግዛት ጽንሰ ሃሳብ ለመወለዱ በር መክፈቱን ይነገርለታል (Ashcroft, et al. 1995; Tyson, 2006; Dobie, 2012)። በወቅቱ ቅኝ ገዥዎች በጉልበትና በሀይል አገራቱን ከመቆጣጠራቸው ባሻገር ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና ሥነ ጽሑፋቸውን በግድ በመጫን ቅኝ ተገዥዎች ለራሳቸው ባህል፣ ቋንቋና ማንነት እንዲሁም ሥነ ጽሑፍ ያላቸው ግምት እነዲሸረሸር፣ በአንፃሩ ደግሞ ቅኝ ገዥዎቻቸውን አምላኪ እንዲሆኑ ከምጣኔ ሀብት ብዝበዛው ባልተናነሰ ሴራ ተፈፅሞባቸዋል። ሆኖም ቅኝ ተገዥዎቹ ከባርነት ለመውጣት የነፃነት ትግል ማድረግ ከጀመሩበት ጊዜና ከዚያ በኋላ የድህረ ቅኝ ግዛት ዘመን ሊባል የሚችል እንደሆነ ይነገራል፤ ይህንን እንቅስቃሴ ተከትሎም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ የመጨረሻዎቹ አስርተ ዓመታት ውስጥ ድህረ ቅኝ ግዛት የሚለው ቃል ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ (Hans, 2007,.p. 200)።

Hans (2007, p. 200) “በ1980ዎቹ ላይ የጋራ ብልፅግና ሀገራት የሥነ ጽሑፍ ጥናት በአዲስ ብቅ ካሉት ሰፊ የሥነ ጽሑፍ፣ የባህል፣ የፖለቲካ እና የታሪክ መስኮች መካከል አንዱ ለመሆን ቻለ፤ ዛሬ የድህረ ቅኝ ግዛት ጥናት የምንለው” ሲል ጽንሠ ሃሳቡ መቼ መስፋፋት እንደተጀመረ አስፍሯል። ቅኝ ገዥዎች በቅኝ ከያዟቸው ሀገራት ሲለቁ ቋንቋቸውን የበላይ፣ ባህላቸውንም በሀገሬው ሰዎች ዘንደ ተመላኪ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ምዕራቡን ዓለም አምላኪና ናፋቂ አስተሳሰቦችን አፍርቷል። ይህ አስተሳሰብ በአንፃሩ ደግሞ የቅኝ ገዥዎችን አስተሳሰብ በውርስነት ይዘው እንዲቀጥሉ በማድረጉ ኬኒያዊው ደራሲ Ngugi wa Thiong'o *Decolonizing the Mind: The Politics of Language in African Literature* (1986) በሚለው መጽሐፉ እንደሚገልፀው አዕምሮን ከቅኝ ተገዥነት አስተሳሰብ ነፃ ማድረግን አስፈላጊ እንቅስቃሴ አድርጎታል። በመሆኑም ይህንን ለመታገል እና በቅኝ ግዛት ውስጥ የነበሩ ሀገራት ወደራሳቸው ማንነት በመመለስ በራሳቸው ቋንቋ እየፃፉ፣ የራሳቸውን ባህልና ወግ እያስተዋወቁ ከአዕምሮ ቅኝ ተገዥነት እንዲላቀቁ የሚያግዝ ንድፈ ሃሳብ ሆኖ ስለተገኘ ለዘህ ጥናት መተንተኛነት ተመርጧል።

## የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በቅኝ ግዛት እና በድህረ ብቅኝ ግዛት የሥነጽሑፍ ጭብጦችና የትረካ ስልቶች ላይ በኢትዮጵያውያን አጥኝዎች የተሰሩ ጥናቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የማሕሌት አብርሐምን (2006) እና የመላክነህ መንግስቱን (2008) ጥናቶች ጠቅሶ ማለፉ በቂ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አጥኝዎች እስከሚያውቁት ድረስ በመንግሥቱ ለማ ትውኔቶች ላይ የቅኝ ግዛት እና የድህረ ብቅኝ ግዛት ጭብጦችና የትረካ ስልቶችን በመተንተን የተሰራ ጥናት አላገኘንም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ከመንግሥቱ ለማትውኔቶች መካካል *ፀረ ኮሎኒያሊስት* (1975a) በተሰኘው ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል። በዚህ ተውኔት የጣልያን ወረራ ያስከተለውን ተፅዕኖ ለማሳየት ሞክረዋል። በወረራው ሀገሪቱን በጉልበት ቅኝ ለማድረግ ከተፈፀመው ግፍ ባሻገር የአካልም ሆነ የመንፈስ አርበኝነት እና ባንዳነት መሳ ለመሳ መሄድ መቻሉን አሳይተዋል።

የመጀመሪያው የጥናቱ መነሻ ምክንያት፡- ለጥናት የተመረጠው ተውኔት ከድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ አንፃር የተጠና አለመሆኑና ከዚህ አንፃር የጥናት ክፍተት መኖሩ ነው። ሁለተኛው መነሻ ምክንያት በተውኔቱ መነሻነት የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ከድህረ ቅኝ ግዛት ንድፈሃሳብ አንፃር ሊጠና የሚችል መሆንና አለመሆኑን ለመፈተሽ ካለን ፍላጎት ነው።

## የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በሁለት የተከፈሉ የምርምር ጥያቄዎችን አንስቶ መልስ ለመስጠት ይሞክራል። ዐቢይና ንዑሳን ጥያቄዎች በሚልም ተከፋፍሏል። ይሄውም "በተውኔቱ ውስጥ የተን ፀባረቁት ዋና ዋና የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች ምን ምን ናቸው?" የሚለው በዚህ ጥናት ውስጥ በዐቢይ ጥያቄነት የሚነሳ ይሆናል። ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. በተውኔቱ ውስጥ የተንፀባረቁት ዋና ዋና የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች ፋይዳ እንዴት ይገለፃል"?
2. በተውኔቱ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም የድህረ ቅኝ ግዛት አስተሳሰብን በምን መልኩ ያንፀባርቃል?

## የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተውኔቱ ውስጥ የተንፀባረቁት ዋና ዋና የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች መመርመር ይሆናል። ይህን ዋና ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ዝርዝር የጥናት ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፤

1. በተውኔቱ ውስጥ የተንፀባረቁት ዋና ዋና የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦችን ፋይዳ መመርመርና መተንተንና መፈከር ፤
2. በተውኔቱ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም የድህረ ቅኝ ግዛት አስተሳሰብን በምን መልኩ በምን መልኩ እንደሚያንፀባርቅ መፈከር፡፡

## የአጠናን ዘዴና የመረጃ አተናተን ስልት

ይህ ጥናት በቤተ-መጻሕፍት የተወሰነ ዓይነታዊ ጥናት ነው፤ በዋነኝነትም ለጥናት በተመረጠው የመንግስቱ ለማ *ፀረ ኮሎኒያሊስት* ተውኔት የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ ጽንሰ ሃሳብ መገለጫ ጭብጦች እንዴት እንደተከሰቱ ለማሳየት የጥልቀት ንባብ ላይ የተመሰረተ ሥልትና ሂደት ተጋባራዊ ሆኗል። በዚህ የንባብ ሁኔታም የሚጠናውን ተውኔት እና ለመተንተኛነት የተመረጠውን ጽንሰ ሃሳብ ደጋግሞ በጥልቀት በማንበብ ለመተንተን እና ለመተንተኛነት ሊረዱ የሚችሉ ቅንጭቦችን በማውጣት በየይዘታቸው የማደራጀትና የመተንተን ሥራ አከናውናል፡፡

## ንድፈ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመከተል ለጥናቱም በዓላማ ተኰር ሥልት ከተመረጠው ተውኔት የመተንተኛ ንድፈ ሃሳቤን ሊያሳዩ የሚችሉ ቅንጭቦችን በማምጣት ተተንተዋል። በመሆኑም ከተውኔቱ የሚወጡ ቅንጭቦችን ለማጥኛነት ከተመረጠው ጽንሰ ሃሳብ ጋር በማመሳከር ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል።

ስለሆነም ለእዚህ ተውኔት የተሻለ የማጥኛና የመተንተኛ ዘዴ ይሆናል ያልነውን የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብን ተጠቅመናል። በዋነኝነትም የድህረ ቅኝ ግዛት ንድፈ ሃሳብ

*መገለጫዎች ወይም ጭብጦች በሆኑትና ከተመረጠው ተውኔት ጋር ሊተሳሰሩ የሚችሉትን እያወጣን በመተንተን አመሳከረናል። ለጥናት በተመጠው ተውኔት ውስጥ ተቀንጭበው በሚቀርቡ ሃሳቦች ላይ በመመስረት ከአውሮፓ ማዕካላዊነት* (eurocentirism)፣ *ከምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ* (orientalism)፣ *ከባይታወርነት* (Unhomeliness)፣ *ከራስን አለመሆን* (Mimicry)፣ *ከገዥ-ተገዥ ድልድል* (hegemony) *እና ቋንቋ፡-ድምፅ አልባው ጠመንጃ ከሚሉት መገለጫዎች አንፃር ትንታኔ ተሰጧል።*

- *አውሮፓ ማዕካላዊነት (eurocentirism) የአውሮፓ ባህል የሁሉም ነገር መለኪያ እና የከፍታ ደረጃ ማሳያ ነው የሚለል አስተሳሰብና ርዕዮተ ዓለም የሚያራምድ ነው። ይህ አስተሳሰብም በቅኝ ግዛት ዘመንና ከዚያ በኋላ ለረጅም ዘመናት የተሰራበት ትርክት ነው።*
- *የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (orientalism) አፍሪካን፣ እስያን፣ የአረብ ሃገራትን ወይም ደግሞ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት፤ ጨካኝ፣ መጥፎ፣ የማይታመኑ፣ እና ሌሎችንም አፍራሽ መገለጫዎች የሚሰጥ እና ይህ ትርክት እንዲሰርጽ ይሰራል፡፡*
- *ባይታወርነት (unhomeliness) ከራሳቸው ሀገር ባህል እና ማንነት ርቀዋል፤ አውሮፓውያን ደግሞ የእኛ ናቸው ብለው አይቀበሏቸውም፤ በዚህ ምክንያት "እኔ ማነኝ? ከየትኛው ነኝ? ወዴት ልጠጋ?" በሚል መባዘን ምክንያት የባዕድነትና የሀሳብ ወይም የህሊና ማረፊያ ማጣት የሚወልደው ስሜት ነው፡፡*
- *ራስን አለመሆን/አስመሳይነት (mimicry) የአውሮፓ ማዕከላዊነት ዋና ሰለባ የሆኑና በዚያው ያመኑ በመሆናቸው ራሳቸውን እንደ አውሮፓውያን ለማስመሰል ወይም እነሱን መስለው ለመታየት መውደቅ መነሳት።*
- *የገዥ ተገዥ ድልድል (hegemony) ከቅኝ ግዛት ነፃነት በኋላ አፍሪካውያን፣ እስያውያን፣ አፍሪካ አሜሪካውያን ነባር ሕዝቦች፣ እምነት የለሾችና በዝርያቸው ዝቅተኞች አድርጎ የመፈረጅ ሥራ ተጠናክሮ ቀጠለ። ለመገዛት እንጂ ለመግዛት እንዳልተፈጠሩ አምነው* (hegemony) *ሀብታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ማንነታቸውን ሥነ ልቦናቸውን … ለቅኝ ገዥዎች አሳልፈው መስጠታቸውን* Said (1978) *አስፍሯል።*

*ቋንቋ፡-ድምፅ አልባው ጠመንጃ*—*በዚህ የመተንተኛ ጭብጥ በተመረጡት ተውኔቶች ውስጥ የቅኝ ገዥዎች ቋንቋ በምን ያህል ደረጃ ሰርጾ እንደገባ የማሳይበት ይሆናል። ይህ ጭብጥ የቅኝ ገዝዎች የሁሉም ነገር የበላይ የመሆን ፍላጎት የሚተላለፍበት ዋነኛው መሣሪያ በመሆኑ ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ ውሏል።* Ngugi (1994፡3) *ይህንን የቋንቋ ወረራ ጠንከር አድርጎ ሲገልፀው የባህል ማውደሚያ ቦምብ ይለዋል። ይህ ቦምብ ደግሞ ነባሩ ሕዝብ በነባር ቋንቋው የሚገለጡትን የሰዎች ሥም፣ ራሱ ቀንቃውን፣ ቦታዎችን፣ የትግል ታሪካቸውን፣ አንድነታቸውን እና አቅማቸውን የማፈራረስ ሥራ መሥራቱን አስፍሯል* (Ngugi,1994፡3)። *በመሆኑም ከእነዚህ ጭብጦች አንፃር ተውኔቱን በመተንተን ለማጥናት ተሞክሯል።*

## የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦች ትንተና በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ተውኔት

### 1. የአውሮፓ ማዕከላዊነት (Eurocentirism)

*የአውሮፓ ምዕከላዊነት አውሮፓ የሁሉም ነገር መነሻ መድረሻ ናት ብሎ የሚያምን ነው። ሁሉም ነገር ከአውሮፓ፤ ከአውሮፓም ከእንግሊዝ ይነሳል የሚል ትርክት ይዞ ይህ ምስል እንዲሰርፅ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማል። በመንግስቱ ለማ ፀረ ኰሎኒያሊስት ተውኔት ይህንን*

የድህረ ቅኝ ግዛት ንድፈ ሃሳብ መገለጫ በስፋት ማግኘት ተችሏል። ለማሳያነት የማቀርባቸው ቅንጭቦች በአንድ በኩል የአውሮፓ ማዕከላዊነትን የሚደግፉና የሚያቀነቅኑ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን የሚቃወሙና የሚሞግቱ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ትንተናውን ከተውኔቱ ማሳያ በማቅረብ እንጀምራለን፤

> በአሁኑ ወቅት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ አምፔሪያሊስት፣ ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት የሆነ አቋም ይዞ በአብዮታዊው መንግሥት መሪነት በኅብረተሰባዊነት ጎዳና በሚራመድበት ጊዜ የፋሽስት ኰሎኒያሊዝምን የቅኝ ግዛት ቀምበር ለመሰባበር ለሚዋጉትና ለሚታገሉት ለዚምባብዌ ፣ ለናሚቢያና ለደቡብ አፍሪቃ የነፃነት ንቅናቄ አርበኞች የማያወላውል ድጋፉን ሰጥቷል፡፡
>
> ከዚህ አንፃር ሲታይ ይህ ተውኔት በራሳችን ላይ ቀድሞ የደረሰውን በማስታወስ በእነሱ ላይ ባሁኑ ጊዜ የሚፈፀመው ግፍ በይበልጥ ያሳስበናል፤ በመንፈስ ያስተባብረናል፡፡
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 17)

የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ አንድ መገለጫ የሆነዉ በቅኝ ግዛት ሥር ያሉ ሀገራት ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ማደራጀት፣ ማነሳሳት፣ ማስተባበር፣ መምራት ነው፡፡ በዚህ አንፃር ሲታይ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሀሳብ ኢትዮጵያ በአምስት ዓመቱ የጣልያን ወረራ ወቅት በአርበኞቿ ተጋድሎ መልሳ ነፃነቷን ብታገኝም የደረሰውን በደልና ግፍ ግን የሀገሬው ሕዝብ አይረሳውም፡፡ ነፃነት ማጣት ምን እንደሚመስልና ምን ያህል አስከፊ እንደሆነም ያውቀዋል፡፡ በመሆኑም የነፃነት ማጣት ምን ማለት እንደሆነ የተረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ለሚታገሉት ዚምባብዌ፣ ናሚቢያ፣ ደቡብ አፍሪካና መሰል ሀገራት የመንፈስ ድጋፉን እንደሚያደርግ በተራኪው ካሴ በመድረክ ሁኔታ መግለጫው ተገልጿል፡፡

የካሴ ትረካ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን ያለመቀበል ቅስቀሳም ነው። በአውሮፓ ማዕከላዊነት ላይ በማመፅ ለነፃነት የሚደረግን ትግል የሚደግፍ፣ የሚያደራጅ፣ የሚያስተባብርና የሚመራ ሃሳብ በማንሸራሸር በቅኝ ግዛት ቀንበር ሥር ሆነው በነፃነት ማጣት ሲሰቃዩ ለነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ድጋፉን ሲሰጥ እንታዘባለን፤

> ለጥቆ አንድ አጭር ሰው፤ ግምባረ ገለጣ እንደማነከስ እንደመሮጥም እያለ ይመጣና ሽማሌው አጠገብ ሲደርስ ይቆማል፤ ዕድሜው ከሃምሳ አያንስም፤ ነጠላ አልደረበም፤ እጀ ጠባቡ አሥር ቦታ የተጣጣፈ በመረሬ፣ በጭቅቅት፣ በላብ የተለወሰ ነው፡፡ ጐንጩ ጐድጉዶ የፊቱ አጥንት ገጧል፡፡ እጅና እግሩ ሳር ነው፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 22)

በዚህ የመድረክ ሁኔታ መግለጫ የተገለጠው በተውኔቱ ውስጥ አንድ ባለታሪክ የሆነው የኢትዮጵያዊው ሊቅ የውሂብ ገጽታ ነው፡፡ ውሂብ በአብነት ትምህርት የበቃ ነበር፡፡ ግን ግዥዎቹ አውሮፓውያን ሀገሩን እንዳይጠቅምበት አደረጉት፡፡ "ዕውቀት፣ ሥልጣኔ፣ ጥበብ፣ ሳይንስ መነሻ ማዕከሉ ከእኛው አውሮፓ ነው" በሚለው አመለካከታቸው በውሂብ የተወከሉት መሰል በሀገር በቀል ዕውቀትና ጥበብ የተሞሉት ኢትዮጵያዊውያን ቦታ አጡ፤ ተዋረዱ፤ ተጐሳቆሉ፤ የዓመት ልብሳቸውን እንኳ በወጉ መልበስ ተሳናቸዉ፤ የዕለት ጉርሳቸውንም በልመናና ከአውሮፓውያኑ ቅኝ ገዥዎች ወኪል ከጣልያን በመለማመጥ፣ በማጐብደድ የሚያገኙ ሆኑ፡፡ ይህም ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌላው የምሥራቁ ዓለም ክፍል በኑሮው ጐስቋላ፤ ኋላቀር ብሎ የሰየመውን ተግባራዊ የማድረግ ሂደት እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ የሁሉ ዕውቀትና የጥበብ ንድፈ ሀሳብ መነሻና ማዕከሉ አውሮፓ ነው፤ ሁሉም ነገር ከአውሮፓ ይነሳል፤

"ወዳልሰለጠነው" ዓለምም ይሰራጫል" ብለው የአውሮፓ ማዕከላዊነትን እያፀኑልን እንደሆነ መገመት ይቻላል፤

> ሽማግሌ ፡- እስከ መቼ፣ እስከ መቼ፣ እስከ መቼ ድረስ ቸል ትለኛለህ?
>
> ፓጆ፡- ፓርካ-ላሚዜሪያ!
>
> (አንገታቸውን ጨምድዶ በኃይል ጐትቶ ያነሳቸዋል፡፡ ቀኝ እጃቸውን በግድ ወደ ላይ ይሰቅለዋል።)
>
> ሳሉታ ኰሎኒያሊስትዚ! - ሳላምታ - አላ ማኒዮራፋስታ ሳላምታ!
>
> ሽማግሌ፡- (ይባንናሉ) ምን አድርግ ነው?
>
> ፖጆ፡- (ያምባርቅባቸዋል) ሳሉታ!
>
> (ራሱ የፋሺስት ሰላምታ ሰጥቶ አሰጣጡን ያሳያቸዋል፡፡ ግራ ገብቷቸው እጃቸው ከግምባራቸው ይወርዳል፡፡ ሦልዳቶው ይብስበታል፤ በሽማቸው አንቆ ሲያርገፈግፋቸው የያዙት ጭራ ከመሬት ይወድቃል፡፡) ምላሱን ጐልጉሎ "ጡጥ" ብሎባቸው መንገዱን ይቀጥላል።
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 22)

በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንኳን የሰባ ዓመት አዛውንት በትንሹ በዕድሜ የሚበልጥንም ማክበር የኖረ ባህል ነው፡፡ መደገፍ፣ ማክበር፣ መቀመጫ ወንበር ቀድመው እንዲያገኙ ከተቀመጡበት ተነስቶ የራሱን ወንበር በመጋበዝ ማስተናገድ፤ ለምግብ ሲቀርቡ አጐንብሶ እጃቸዉን ማስታጠብ፤ ወደ ምኝታ ሲያቀኑ እግራቸውን ማጠብ የተለመደ ባህል ነው፤ ሲኞር ፓጆ ግን ይህንን የቆየ ትውፊትና ባህል ሲሰብረው፣ ሲያዋርደው እንመለከታለን፤ የሰባ ዓመቱን አዛውንት በሽማ አንቆ እንደ ዶሮ ወደ ላይ አንስቶ ማርገፍገፉ ለሕሊና የሚከብድ ነው፡፡

በምእራብ አውሮፓ የተጠቀመው ስልት ቋንቋን በመጠቀም የራሳቸውን ባህላዊ እሴቶች ከፍ ለማድረግ እና ምስራቃዊ ናቸው የሚባሉትን እየቀነሱ ነው። ይህ ብዙውን ጊዜ የተከበሩ ምስራቃዊ ሰዎች እንደ ዝቅተኛ ወይም የማይገባቸው አድርገው ሲገልጹ፣ በተለይም እንደ መሳለቂያ እና መሳቂያ ባሉት ዘዴዎች ይገለጻል።

> ሽማግሌ ፡- … ያንን የመሰለ ደወል ጣልያኖች እለት እለት ይወግሩታል፡፡ ጨኸቱን ሆዴ አልቻለውም፡፡ አንዳንዴ ነፍሰ ገዳይ ከቁራኛ አምልጦ ታቦት ሊማጠን የሚደውለው ይመስለኛል፡፡ አንዳንድ ቀን ደግሞ ሰው ሞቶ ለፍታቱ ካህናት ለመሰብሰቢያ የሚደወል ይመስላል፡፡
>
> ውሂብ፡- የሞተው ያበሻ ነፃነት ነው፡፡ ክብራችን ነው የሞተው፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 24)

እዚህ ላይ የሁለቱን ሰዎች ንግግር ብናጤነው የአውሮፓ ማዕከላዊነትንና የበላይነትን ለማንገስ ሲባል የማንነታቸው፣ የባህላቸው፣ የወጋቸው፣ የትውፊታቸው፣ የሐይማኖታቸው መደፈርና መዋረድ አንገብግቧቸዋል፤ ነፃነታቸውን ማጣታቸው በሐዘን እርር ኩምትር እንዲሉ አድርጐታል፡፡ ነፃነት ተገፍፎ ምን ክብር አለ እያሉን ነው፡፡ በተለይ የወሂብ ንግግር ነፃነት ከሌለ ክብር ስለሚባለው ጉዳይ ማሠቡ ዋጋ የለውምና ነፃነቱን ለማስመሰል መነሳት እንዳለበት እያነሳሳ ነው፤ የድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ አንዱ መገለጫ የሆነው በቅኝ ግዛት ሥር ያሉ

ሀገራትን ሕዝብ ለነፃነት ማነሳሳትና ተሥፋ እንዲሰንቁ ማድረግ የሚለውን ሃሳብ በጥቅሱ ውስጥ እናገኝበታለን፡፡

ባህላቸው ተዋርዷል፣ ሃማኖታቸው ተንቋል፤ ፈርሷል፤ ትውፊትና ወጋቸው እንዳልነበረ እየሆነ በቅኝ ገዥዎች ምዕራብ አውሮፓ ወኪል በሆነው የጣልያኑ ሲኞር ፓጆ እና ሌሎች የፋሽስት ግብረ አበሮች ከነባሩ ማህበረሰብ ህሊና ለማስወጣት የሚደረገውን የባርነት አካሄድ መቀበል ክብር ማጣት ነው እያሉን ነው፤ ስለዚህ የአውሮፓ ማዕከላዊነት (eurocentirism) አስተሳሰብን እየተቃወመ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የእኛ (የምዕራብ አውሮፓ) ባህል፣ ወግ፣ ትውፊትና ሃይማኖት ብቻ ነው ልዕለ ኃያል መሆን ያለበት የሚለውን አስተሳሰብና ትርክት መቀበል ክብርን ማጣት ነው፤ ከዚፊህ ደግሞ ለነፃነት መነሳት ግድ እንደሚል እየጠቆመን ነው፡፡

## 2. *የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ* (Orientalism)

*በመንግስቱ ለማ **ፀረ ኰሎኒያሊስት** ሌላው ጎልቶ የሚታየው የአውሮፓ ማዕከላዊነት ማራመጃ ዋና ትርክት የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ* (orientalism) *ነው*። Edward Said (1978) *የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ* (orientalism) *በሚለው ጽንሰ ሀሳቡ ቅኝ ገዥዎች (ምዕራብ አውሮፓ) ዓለሙን የሰለጠነና ኋላቀር በማለት በሁለት ጎራ ፈርጀው አፍሪካን ጨምሮ ምሥራቁን የዓለም ክፍል በአላዋቂነትና ኋላቀርነት መድቦ ይህን ስዕል እንዲጐላ በተለያየ መንገድ ያሰርፃል፤ "የቤተ ክርስቲያኑ ደወል ቅጥ በሌለው ያላዋቂ አደዋወል ሲላጋ ጆሮ ያደነቁራል፡፡"* (*መንግሥቱ*፣1975a፣*ገጽ* 17) *ይህ አስተሳሰብ የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃን ትርክት የሚያሳይ ነው፡፡ ከፍ ብለን ከፀረ ኰሎኒያሊስት በጠቀስነው ቅንጭብ ሀሳብ እንደምንረዳው በአማኙ ዘንድ ከፍተኛ ክብር ያለውን የቤተ ክርስቲያኑን ደወል ሲኞር ፖጆ ሥርዓቱን ባልጠበቀ መልኩ በፈለገው ሰዓት ይደውለዋል፤ ከአውሮፓ ውጭ የሆነውን ማንነት፣ ትውፊት፣ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ… በማራከስ ምርጡና የሰለጠነው ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ትውፊት… የአውሮፓ ነው የሚል መልዕክት እያስተላለፈበት ነው። ደዋዩ የፋሽስቱ ጣልያን ወታደር ሲኞር ፓጆ ነው፡፡ ስለዚህ ሲኞር ፓጆ የኋላቀርና የአላዋቂ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ትውፊት… ነው ብሎ በማመኑ በተከበረው ቤተክርስቲያን ውስጥ ለቅዳሴና ለሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት መገልገያ የሆነውን ደወል እንደፈለገው ሲወግረው እናስተውላለን፡፡*

*አውሮፓውያኑ በጦር ኃይል ከጫኑት ፖለቲካ ባሻገር በነባሩ ባሕል፣ ትውፊት፣ ማንነት፣ ሃይማኖት ላይ ለሚፈፅሙት በደል፣ ማሳያ ሊሆን የሚችል ጥቅስ ነው፡፡ የደዋዩ ተግባር "ሥልጡኑን" አውሮፓ፣ "በሁሉ እውቀቱ" ቀዳሚ ነኝ ባዩን አውሮፓ ቦታውን አስለቅቆ ከኋለኞቹ ተርታ የሚያሰልፍ ነው፤*

> *ሽማግሌ፡- "የልጅ ለማኞች - እናት አባታቸው ጠፍተውባቸው - ከሩቅ ሀገር ተሰደው የመጡ- ይለምናሉ፡፡ (በጭራው ያመለክታሉ) እዚያ ታች ሶልዳቶው ሁሉ ግብር ይበላል፡፡ "ሜንሳ" ይሉታል፤ ድንኳን አዳራሹን፣ ሕፃናቱ እዚያው ሄደው ይኰለኰላሉ፡፡ ኩሊ አይሆኑ መንገድ አይሠሩ፣ አቅሙ ጠፋ፡፡ በምን አቅም፣ ጣልያኑ ሲያሰኘው ፍርፍሪ ይጥልላቸዋል፡፡ የጠጣ ኑሮ ነው የገደል ዝንጀሮ፡፡ ያገኙትን ይበላሉ የአሳማ ሥጋ አልቀራቸውም"፡፡*
>
> (*መንግሥቱ*፣1975a፣*ገጽ* 21)

*ይህ ንግግር አፍሪካን ጨምሮ ምሥራቁ የዓለም ክፍል ኋላ ቀር፣ ደሀ፣ የማይጠቅም አድርገው መሳላቸውን ማሳያ ነው፡፡ ይህንን እሳቤያቸውን ለማሳካት የሀገሬውን ሕዝብ እያስለሙኑ ያበላሉ፡፡ ልመና የሀገሬው ሕዝብ መገለጫ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ሕፃናቱም በለጋ ዕድሜያቸው በወላጆቻቸው ቤት ውስጥ ሆነው ማደግ ሲገባቸዉ የጣልያንን ፍርፋሪ ተስፋ አድርገው*

የሚኖሩ ባዛኝ ሆነዋል፡፡ የመኖርና ያለመኖር ዕጣ ፋንታቸዉ የሚወሰነው ጣልያኖች በሚወረውሩላቸው የምግብ ትራፍራፊ ሆኗል፡፡ ይህ ድርጊት የሀገሬውን ሕዝብ ክብር ዝቅ ለማድረግ፣ የወረደ ነው ለማለት የተጠቀሙበት ነው፡፡

ይህም አልበቃ ብሎ ሲያሻው ይባርራቸዋል፣ ሲያሻው በድንጋይ ያሯሩጣቸዋል፤ ኑሯቸው ከሰው በታች ወረደ፤ ከገደል ዝንጀሮ ጋር አቻ ሆነ፡፡ የሚበሉት የሚቀምሱት የሚልሱት ከማጣታቸው የተነሳ በሀገሪቱ ሕዝብ ዘንድ ነውር የሆነውን የዓሳማ ሥጋ ሁሉ እስከመብላት ደርሰዋል፡፡ “ሕይወትን ሰጭም ነሽም እኛ (ጣልያኖች) ነን” እያሉ ነው፡፡ ጣልያኖች ደግሞ የምዕራብ አውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ወኪል ናቸው፡፡ የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃን (orientalism) እያሳዩ ነው፡፡

*ሽማግሌ ፦ "ሆነ - ሆኑ፡፡ ገናናው የኢጣልያ [ጣልያን] መንግሥት የሮማን ብርሃን እንዲህ እያደረገ ያበራልናል፡፡ ምን ይሏል? ያውሮፓ ሥልጣኔ ነው"* [*አፅንኦት የእኔ*] (*መንግሥቱ*፤ 1975a፣*ገጽ* 21)፡፡ እኛ (*ምዕራብ አውሮፓ*) ስልጡኖችና የዓለም የሥልጣኔ ብርሃን እነሱ (ጥቁሮችና *ምሥራቁ ዓለም*) ኋላ ቀሮች፣ ከሥልጣኔ ወደ ኋላ የቀሩ በማለት የሚተርኩትን እያሽሟጠጡ ሃሰት መሆኑን እየነገሩን ነው፡፡ ሽማግሌው ቢሰለጥኑ ኖሮ፣ የሥልጣኔ ብርሃን አብሪዎች ቢሆኑ ኖሮ፣ እንዲህ ጨካኝ አይሆኑም ነበር፤ ግፈኞች አይሆኑም ነበር፤ የሚል ሀሳብን በማራመድ የምዕራብ-ምሥራቅ የፍረጃ (orientalism) አስተሳሰብን ያፈርሱታል፡፡ ንግግራቸው ያልሰለጠኑት፣ ያልዘመኑት፣ ዕውቀት አልባዎቹ ቅኝ ተገዥዎቹ ሳይሆኑ በወራሪዎቹ ጣልያን የተወከሉት ቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓውያኑ ናቸው የሚል አንድምታ አለው፡፡ ሽማግሌው በዚህ ንግግራቸው በምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (orientalism) ጽንሰ ሃሳብ ለምሥራቁ ዓለም (ማለትም በቅኝ ተይዘው ለነበሩት ሀገራት) የተሰጠውን ፍረጃና የተሳሳተ ምሥል ተገቢነቱ ለምዕራቡ ዓለም ነው እያሉ መሆኑን እንረዳለን፡፡ እኒህ ሽማግሌ በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* (1975a፣*ገጽ* 21) ላይ ሌላም በቅኝ ለተያዙት ሀገራት የተሰጠውን በአሉታ የተሞላ ፍረጃ ማፍረሻ ሀሳብ ያመጣሉ፤

> ሽማግሌ ፡- *ፖጆ ፖጆ ሲኞር ፖጆ* - የሚባለው ይህ ነው፡፡ የመንገድ ሰራተኞች አለቃ - *አምላክ ሲወገር ድንጋይ ያቀበለ፣ ያልፈነከተው ሰው የለም፡፡ በቡጢ ያወለቀው መንጋጋ ቁጥር የለውም፡፡ ያረገፈው የሀበሻ ጥርስ በእንቅብ ይሠፈራል*፡፡ የእርግጫው ስሙ "ካቻን ኩሎ" ይባላል አሉኝ ልጆቹ። [*አፅንኦት የእኔ*]
>
> (*መንግሥቱ*፣1975a፣*ገጽ* 21)

የአፅንኦት ምልክት የተደገባቸው ሀሳቦች ቅኝ ገዥዎቹ በቅኝ ተገዥዎቹ ላይ የፈጠሩትን ሀሰተኛ ምስል የሚሰርዝ ነው፡፡ ምስሉ እውነት በሚሉት ማጥፊያ ሊጠረግ የሚችል ነው እያሉን ነው፡፡ በSaid (orientalism) ጽንሰ ሀሳብ ምዕራብና ምስራቅ ተብሎ የተከፋፈለውን ዓለም ፍረጃ ቦታ የሚቀያይር ነው፡፡ በሰብዓዊነት ደረጃው ከፍ ያለ፣ በሥልጣኔው ልዕለ ኃይል የሆነ፣ በዝርያው ጥራት የተመሠከረለት፣ ልዕለ ሰብ ብሎ ራሱን የፈረጀው ቅኝ ገዥ ጐራ ለራሱ ደጋግሞ የተረከው ትርክት እውነተኛ ቢሆን ኖሮ ወኪሎቹ ወራሪዎቹ ጣልያናዊውን ሲኞር ፖጆን ያህል ጨካኝ እና አውሬ ባልሆኑ ነበር፡፡ በጥቅሱ ውስጥ ያሰመርሁባቸው ሀሳቦችም የሚባለው ሌላ የሚሆነው ሌላነቱን ማሳያ ነው፡፡ "*ያረገፈው የሀበሻ ጥርስ በእንቅብ ይሰፈራል*" የሚለውን ስናነብ አፍሪካን የሥልጣኔ ብርሃን ልፈነጥቅባት ነው የመጣሁት የሚለውን ውሸትነትና ከንቱነት እንገነዘባለን፡፡

"አምላክ ሲወገር ድንጋይ ያቀበለ፡፡" የሚለውስ ምን መልዕክት ይነግረናል? ያው ጨካኝነትን፣ አውሬነትን እንጂ፤ ስለዚህ ሽማግሌው ሮማን የሥልጣኔን ብርሃን በስም እንጅ በተግባር

አላየችውም፤ የዓለም የሥልጣኔ ብርሃን ሊሆኑ ቀርተው የነባሩን ሕዝብ የሥልጣኔ ጭላንጭልም ጭራሹን እያጨለሙት፤ ጭላንጭል ብርሃኑ ተስፋፍቶ ወገግ እንዳይል እያዳፈኑት ነው የሚል አንድምታ እናገኝበታለን፡፡

አውሮፓውያኑ ወራሪዎች ከራሳቸው ባሕል፣ ትውፊት፣ ሃይማኖትና ማንነት ባለፈ የሌሎችን በማውደም፣ በመበረዝ የታወቁ እንደሆነም በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ላይ እናገኛለን፡፡ የቅኝ ገዥዎቹ ባሕል ፍፁምና የተዋጣላት፤ የዓለሙ ሁሉ ባሕል መሆን አለበት ብለው የሚሰብኩ፣ የቅኝ ገዥዎቹ ትውፊትና ሃይማኖትም እንከን አልባ ነው ብለው ለዓለሙ ሁሉ የሚለፍፉ በመሆናቸው በቅኝ ግዛቶቻቸው ሥር ያለውን ነባር ባህል፣ ትውፊት፣ ማንነትና ሃይማኖት ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ እንረዳለን፤

> ሽማግሌ፡- "ምናለ፣ የቤተክርሲያን ደዋይ ሲኞር ፖጆ ሆኗል፡፡ ለኩሊዎቹ ሥራ መግቢያና መውጫ ምልክት አድርጎታል፡፡ ጠዋት በአንድ ሰዓት፣ በእኩለ ቀን፣ በስምንት ሰዓት፣ ሲመሽ በአስራ ሁለት ሰዓት፣ በቀን አራት ጊዜ ያን የመሰለ ደወል ይጫወትበታል፡፡ ሊሰብረው ነው፤ ይህ መዶሻ ራስ፤ ዶጮ ዶለዝ፡፡
>
> (መንግሥስቱ፣1975a፣ገጽ 21)

ለራሳቸው የሰጡትን የሰብዕና እና ባህሪ መገለጫ በተግባር ለማስመሰል የግድ የነባሩን ማኅበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ማንነት፣ ትውፊትና ሐይማኖት ማፍረስ፣ ማዋረድ፣ ማጣጣል፣ እንዳለባቸው ከሲኞር ፖጆ ድርጊት እንረዳለን፡፡

በሌላው ጐን ከተመለከትነው የሽማግሌው ንግግር ምዕራብ-ምሥራቅ (Orientalism) ተብሎ በሁለት ተፃራሪ ማንነት፣ ባህል፣ ወግ ትውፊትና ሃይማኖት እንዲሁም ሰብዕና የተፈረጁትን ጐራዎች ትርክቱን የሚገለብጥ ነው፡፡ *"ይህ መዶሻ ራስ፤ ዶጮ፤ ዶለዝ"* በማለት አላዋቂነትን፣ ዕውቀት አልባነትን፣ የአዕምሮ ሥልጣኔ አልባነትን በሲኞር ፖጆ አሳቦ ለቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓ እየሰጡልን ነው፡፡ ይህም አዕምሮን ከህሊና እሥር ነፃ የማስፈታት (Decolonizing the mind) አንዱ ማሳያ ሊሆን ችይላል፡፡

ውሂብና ሽማግሌው ገዥዎቹ የምዕራብ አውሮፓ ቅኝ የማድረግ ዋና ዓላማው ላልሰለጠነው ዓለም የሥልጣኔ ብርሃን ለመፈንጠቅ ነው የሚለው ስብከት ፍፁም ከእውነት የራቀ መሆኑንም ከመግለጽ አይመለሱም፡፡ የሚሉት ሌላ የሚተገብሩት ሌላ መሆኑንም በማሳያ ያስረዳሉ፡፡ የነባሩን ሕዝብ ባህል፣ ወግ፣ ማንነት፣ ትውፊት እና ሃይማኖት ከማፈራረሳቸው ባለፈ ቅርስ መዝረፍ፣ ሀብት መሻማት፣ የሰው ሀገር ታሪክ በመሻማትና መገለጫዎቹን ከሀገሬው ሕዝብ በመሰወር የራስ የማድረግ ተልዕኰን ይዘው የሚንቀሳቀሱ እንደሆኑ በቀጣዩ ንግግራቸው ያሳዩናል፤

> ውሂብ፡- የነበረዎስ አንድ ቤት ሙሉ ብራና መጽሐፍ፣ ያስታውሳሉ ከቀለም አባቶች፣ አያቶች፣ ቅድማያቶች ሲወርድ የመጣው፤ የስንቱ ሊቃውንት ቅርስ፤ ያሁሉ የታለ ዛሬ?
>
> ሽማግሌ፡- ሁሉም ሄደ፡፡ ወሰደው፡፡ ሮማ ገባ…
>
> ውሂብ፡- (ስሜቱ ይቀሰቀሳል) አበቃ፤ ይቅር፤ የድሮውን አናንሳው አንባዬ ይመጣል፡፡ ልሂድ…
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 24)

ብዙ ምስጢር፣ ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ዕውቀት፣ ብዙ ማንነት፣ ብዙ ትውፊት… የያዙት የኢትዮጵያውያን የብራና መጻሕፍት በወራሪው ቅኝ ገዥ ጣልያን ተዘረፉ፣ ወደ ሮማ ተጋዙ፤

የነባሩን ሀገሬ ሕዝብ ታሪክ፣ ቅርስ የማውደም፤ የማጥፋት ሥራ ማከናወን የቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓ ዋና ተግባር ለመሆኑ ወኪል ሆና በቀረበችው ጣልያን እንረዳለን፡፡

በፍረጃ (Orientalism) ጽንሰ ሀሳብ በያዘው ትርክት ልክ የምስራቁ ዓለም (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ከተፈረጁበት ቦታ ላይ የግድ እንዲገኙ ታሪክ አልባ፣ ቅርስ አልባ፣ ሀብት አልባ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፤ እናም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የውሂብና የሽማግሌው ንግግር አማካኝነት የሀገሬውን ነባር ዕውቀት፣ ጥበብ፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና፣ ሳይንስ የያዙትን ብራና መጻሕፍት እየዘረፉ ወደ አውሮፓ መላክ፣ ማውደምና ከሀገሪው ሕዝብ ዘንድ ደብዛቸውን ማጥፋት ትልቁ ሥልት መሆኑን እየነገሩን ነው፡፡ ይህንንም ወራሪዋ ቅኝ ገዥ ጣልያን በተግባር መፈፀሟን አሣይተውናል፡፡

ከዚህ ባለፈ በውሂብ ንግግር ውስጥ የምንረዳው የነፃነት ናፍቆትና ነፃነትን ማጣት ምን ያህል ልቡን እንዳደማው፤ ልቡ ነፃነቱን ለማሥመለስ መሸፈቱን፤ ሁልጊዜም የሀገሩን ነፃነት በልቡ ይዞ የነፃነት ጊዜውን የሚጠብቅ መሆኑን እንረዳለታለን፡፡ የሀገር ፍቅር ስሜቱ ምን ያህል ደረጃ ላይ እንደደረሰና የነፃነት ማጣት ቁጭት እንደተዳፈነ ፍም እሳት ሆኖበታል፡፡

*የፀረ ኮሎኒያሊስቱ* ሽማግሌው በአውሮፓ ማዕከላዊነት (Eurocentirism) ላይ ከመሳለቅ አይመለሱም፡፡ ፍረጃን (Orientalism) የሚያፈርስ ሀሳባቸውን ከመሠንዘር ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ለምዕራብ አውሮፓ የተሠጠው ቦታ ስህተት ነው! የሌላቸውን ማንነትና ሰብዕና ነው ለራሳቸው የሰጡት በማለትም ሲሞግቱ ይታያሉ፤

ሽማግሌ፡- (በግጥም አነጋገር) ካቻንኩሎ

ካቻን ኩሎ፡፡ የጣልያነን በትር እርግጫ

የሮማ ብርሃን መግለጫ፡፡

(መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 25)

ከዚህ ንግግራቸው የምንረዳው የቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓ ወኪልነትን ይዛ የምትንቀሳቀሰው የሮማ የሥልጣኔ ብርሃን መገለጫው ካቻን ኩሎ የሚባለው እርግጫና በትር መሆኑን ነው፡፡ የምሥራቁን ዓለም ክፍል ከሰውነት አውርደው ወደ ጨካኝና እንስሳነት የመደቡት ትክክለኛ እንዳልሆነና ይልቁንም ይህ ትርክት መሰጠት ያለበት የሥልጣኔ ብርሀንን ለመስጠት ነው የመጣሁት እያለች ኢትዮጵያውያንን በጭካኔ ለምትበዘብዘው ጣልያን ነው መሆን ያለበት የሚል ሽሙጥ አዘል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡ የሮማ የሥልጣኔ ብርሃን … ወገግታው የሚገለጠው በድብደባ፣ በማንገላታት፣ መሆኑን በመግለጥ ፍረጃን (Orientalism) ገልብጠው ለምዕራብ አውሮፓዎቹ ይሠጧቸዋል፡፡

ውሂብ በሀገረሰብ እውቀትና ጥበብ የተካነ፣ ነገር ግን በጣልያን ወረራ ምክንያት ያለቦታው የተገኘ ሰው ነው፡፡ ውሂብ የቀለም ትምህርት የቀሰመ ሆኖ እያለ ለጉልበት ሥራ ተዳርጓል፤ ለኩሊነት፡፡ ሆኖም ይህ አያሳስበውም፤ ነፃነቱን አጥቶ የጣልያን ቅጥረኛ ከሚሆን ለምኖ መብላትን መርጧል፤

ውሂብ፡- እለምናለሁ፡፡ በልጅነቴ ተማሪ ቤት ሳለሁ ለምኛለሁ፡፡ በጐንደር፣ በጐጃም፣ በላስታ፣ በበጌምድር፣ በደብረ ዓባይ፣ በደብረ ሊባኖስ ደበሎ ለብሼ ለምኛለሁ፡፡

ካሴ፡- እውነትህን ነው፣ ኩሊነት ላንተ ተስማሚ አይደለም፡፡ መሥራት የሚገባህ የአዕምሮ ሥራ ነበር እንጂ፣ የጡንቻ ሥራ አይደለም፡፡ ተሞሮ በተማሩት መስመር ካልተሰማሩ የጋን መብራት ሆኖ መቅረት ነው፡፡

ውሂብ፡- ኩራዝነቱስ አልቀረልኝም፡፡

(መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 28)

የሀገረሰበ እውቀትና ጥበብ ዋጋ አጣ፤ በወራሪዎቹ ቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓውያን ዘንድ ክብር አልባ ሆነ፡፡ ሁሉም ነገር መነሻው ምዕራብ አውሮፓ የሚለውን ትርክት ተግባራዊ ለማድረግ ሥለሚያስፈልጋቸው ያልሰለጠነ ካሉት የዓለም ክፍል የሚነሳን፣ የሚቀዳን ጥበብና ዕውቀት ጥቅም ላይ አያውሉም፤ እንዲያውም የሞራል ውድቀት እንዲደርስበት እያደረጉ ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ ማድረግ ዋና ተግባራቸው ይመስላል፡፡

ውሂብ የደረሰበት ይሄው ነው፡፡ በአብነት ትምህርት ቤት ተምሮ የጠለቀ ዕውቀት ኖሮት የመጨረሻው ሕይወቱ የጉልበት ሥራ ሆኗል፡፡ መንገድ መቆፈር፣ መሸከም ዕጣ ፈንታው ሆኗል፡፡ ዕውቀት ለተጠሙት የተራራ ላይ ሙብራት መሆን ሲገባው በጋን ውስጥ ቀርቷል። ጣልያኖች የነ ውሂብን ዓይነት በሀገረሰብ ዕውቀትና ጥበብ የተካኑትን በዕውቀታቸው እንዲያገለግሉ ካደረጉማ የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (Orientalism) ትርክታቸውን አፋለሱት ማለት ነው፡፡ የነውሂብን ዕውቀት ከተጠቀሙ አላዊቂና የማያመዛዝኑ ያሏቸውን ኢትዮጵያን ጨምሮ የምሥራቁን የዓለም ክፍል በምዕራቡ አውሮፓ ቦታ አስቀመጧቸው ማለት ይሆናል፡፡ ሥለዚህ ሂሳብ ሰርተው፣ ሥጋ አልብሰው ለዓለሙ የተረኩት የተሳሳተ ምስል ቀለሙ እንዳይለቅ የግድ ሀገረሰብ ዕውቀትን፣ ጥበብን፣ ፍልስፍናን ማውደምና ማዛበትን ዋና ተልዕኳቸው አድርገው መውሰዳቸውን እንረዳለን፡፡ ጣልያኖች የተማሩትንና በረቂቅ እውቀት የተካኑትን ኢትዮጵያውያን የጉልበት ሥራ የሚያሠሯቸው ምሥራቅ ከሚባለው የዓለም ክፍልም ባለዕውቀት፣ ባለጥበብ ሊወጣ አይችልም ከሚለው ሀሳባቸዉ በመነሳት ነው፡፡ ዕውቀትና ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ ሳይንስ… መነሻውም መድረሻውም ማዕከሉ አውሮፓ ነው ለማለት ነው፤

ገብረየስ፡- ምን ታመጣለህ? (እጁን ጐትቶ ካልጋ ሊያወርደው ይሞክራል) ተነስ-ተነስ!

ውሂብ፡- በዱቼ ሙሶሊኒ አምላክ - አንተ ሰው በቪክቶር ቁሳር አማኑኤል አምላክ አትጐትተኝ፡፡፡

(መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 29)

ገብረየስ ለሆዱ ሲል፣ በልቶ ለማደር ሲል ሁሉን ነገር ረስቷል፡፡ ሆዱ ከሞላ የነፃነቱ ጉዳይ አያስጨንቀውም፡፡ በልቶ ለማደር ሲልም በፋሽስቶቹ መሪዎች ለመማል ለመገዘት፣ ለማምለክ እስከ መፈለግ ደርሷል፡፡ በፈጠረው አምላኩ ፈንታ ፍጡሩን የሰው ልጅ ለማምለክ ደርሷል፡፡ ውሂብ የገብረየስ የምድር ላይ ሕይወቱ መቀጠል አለመቀጠል የሚችለው በፋሽስቶቹ ዱቼ ሙሶሊኒ እና በቪክቶር ቁሳር አማኑኤል ቸርነትና ፈቃድ መሆኑን በአሽሙር እየነገረን ነው፡፡ በገብረየስ ውክልና የተሠለፉት መሰሎቹ በፈጣሪያቸው ሥፍራ ፍጡሩን የሰው ልጅ ተክተዋል፡፡ ረሀብ ከሚያሠቃያቸው በፋሽስቶቹ መማል መገዘት መጀመራቸውን ውሂብ እየነገረን ነው፡፡ ውሂብ ደግሞ ከዚህ መፋታት ፈልጓል፡፡ በእነሱ እያመለከ ከሚኖር ልመናን መርጧል፡፡ በባርነት የተሻለ አማርጦ በልቶ ከማደር በነፃነት ለምኖ መብላትን መርጧል፡፡ ውሂብ ለነፃነቱ በጣም ቆርጧል፤ የፈለገው ቢመጣ ነፃነቱን ከማወጅ ወደ ኋላ የሚል አይመስልም፡፡ ይህ ቆራጥነቱና ተስፋውም እሱን፣ ካሴን እና ሸማግሌውን የመሰሉትን ሰዎች የበለጠ የሚያበረታታና የአርበኝነት ትግሉን እንዲያፋፍሙ የሚያደርግ ነው፤

ገብረየስ፡- ሥራ አልሄድም ነዋ?

> ውሂብ፡- አዎ፣ አልሄድም፣ እምቢኝ አሻፈረኝ፡፡ "ዘጠኝ ሞት ቢመጣ አንዱን ግባ በለው" ፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 31)

ይህ አባባሉ ሺህ ጊዜ ፈሪ ሆኖ ከመኖር አንድ ጊዜ ጀግና ሆኖ መሞት የሚለውን ያስታውሰናል፡፡ ባርነትን የመረጠ ሰው ለሆዱ ሲል ሺህ ጊዜ ፈሪ እየሆነ በባርነት መኖርን ይመርጣል፡፡ ውሂብ ደግሞ በባርነት ለመኖር ሺህ ጊዜ ፈሪ ሆኖ ከመኖር ለነፃነቱ የአንድ ቀንን በጀግንነት መሞትን መርጧል፡፡ "እምቢኝ አሻፈረኝ" የአመጽ ጠቃሽ ንግግር ነው፤ የተቃውሞ ጠሪ ሀሳብ ነው፡፡ የኋላ ኋላ ይህ የእምቢተኝነት ጥሪውም ሌሎችንም ማስከተሉን እንረዳለን፡፡

ውሂብና ካሴ የምዕራብ-ምሥራቅ ጐራ ፍረጃን (Orientalism) ትርክት የማፍረስ ሙከራም ሲያደርጉ ይሥተዋላሉ፡፡ በእኛም ያልተማረና ያልሠለጠነ፤ እውቀት የሌለው እንዳለ ሁሉ ፋሺስቶቹም እንደዚያው ሞልቷቸዋል፡፡ እውቀት አልባነትና አለመሰልጠን የተሠጠው ለጥቁሮችና ለምሥራቁ ዓለም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በአብዛኞቹ ቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓውያንም ዘንድ ይህ ችግር እንዳለባቸው ይሞግታሉ፤

> ውሂብ፡- በጣልያን ጊዜ አስማቱ ሁሉ በከሸፈበት፣ መጣፍ ገልጦ እንጀራ የወጣለት ማንን ታውቃለህ?
>
> ካሴ፡- ሸዋ ሳለሁ አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ፋሺስቶቹ ነጭ ቢሆኑ መጣፍ ገላጭ ይንቁ አይምሰልህ፡፡ አብዛኞቹ ከኛው ሰው አይሻሉም፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 38)

የካሴ ንግግር ለምዕራብ አውሮፓ በተሳሳተ መንገድ የተሰጠው ትርክት ሀሰት መሆኑን የሚነግር ነው። እነሱም ያልተማረ አለባቸው፤ እኛም አሉን፤ እኛም የተማሩ የተመራመሩ አሉን እነሱም አሏቸው፡፡ እኛም ኋለቀሮች አሉብን፣ እነሱም እንዲሁ፡፡ እነሱም ጨካኞችና አረመኔዎች አሉባቸው እኛም እንደዚሁ፤ ዋናው ጉዳይ የነጭና የጥቁርነት አይደለም፡፡ ሥለዚህ እዚህ ላይ ፍረጃን (Orientalism) ገደል እየከተተው እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ጣልያኖች ያንን ትርክታቸውን መስበካቸውን አይተውትም፤ ራሳቸውን ሁልጊዜም የሥልጣኔ ብርሃን ማሳያ፣ የሥልጣኔ መሪ አድርገው ይሥላሉ፤ በሰው አመለካከት ውስጥ ለማሥረጽ ደጋግመው ይለፋፍሉ፡፡ ቀጥሎ ያለው የባቲዮኒ ንግግርም የሚያሳየን የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ፍላጐት ላልሰለጠነው የዓለም ክፍል ብርሃን የመፈንጠቅን ተልዕኰ ይዞ እንደሆነም የሚገልጽ ነው፤

> ባቲዮኒ፡- ተረቱን ይተውና፣ ያለንበትን አስገራሚ ጊዜ የዚህን በታምራት የተወለደውን ያዲሱን የፋሽስት መንግሥት ታሪክ ይንገሩት፡፡ የሮማ ብርሀን የድንቁርናን ጭልም መጋረጃ እንዴት አድርጐ እንደቀደደና ይቺ ጥንታዊት አገር ከጥንታዊ እንቅልፏ በገናናው ዱቼ ጠንካራ ቀስቃሽነት ተገድዳ ብንን ብላ ዓይኗን እንደገለጠች ይናገሩ፡፡ "ዓለምን ረስተውት ዓለም ዘንግቷቸው፤ ኢትዮጵያውያን አንድ ሺህ ዓመት ሙሉ እንቅልፋቸውን ለጠጡ"፡፡
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 44)

ይህ ንግግር የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (Orientalism) ትርክት ማሳያ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የድንቁርና ጨለማ በሮማ የሥልጣኔ ብርሃን ተገፈፈ እያለን ነው፡፡ በዚህም ቅኝ ገዥዎቹ ሀገሪቱን የወረሯት ኢትዮጵያን ለማሠልጠን እንጅ ምንም ጉዳይ ኖሯቸው እንዳልሆነ

ለመስበክ እየሞከረ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከኋላ ቀርነት እንቅልፏ በገናናው የሮማ ብርሃን በወለደው ዱቼ ተቀስቅሳ ለሥልጣኔ ብርሀን በቃች እያለ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን ያጠምቃል፡፡ የአውሮፓ ማዕከላዊነት ዋና ማራመጃ የሆነው የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (Orientalism) ጽንሰ ሃሣብንም ተግባራዊነቱን እያሳየን ነው፡፡

በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ውስጥ የምዕራብ-ምስራቅ ፍረጃን (Orientalism) ቦታ የማፍረስ ሃሳቡ በስፋት ሲስተናገድ እናስተውላለን፡፡ ሽማግሌው የሚያራምዷቸው ሃሳቦች ደግሞ ለዚህ ማሳያ ይሆኑናል፤

> ሽማግሌ፡- በምኒልክ ጊዜ እንደዛሬ አልሰለጠናችሁ፡፡ የመርዝ ጢስ እሳተ ገሞራ አልፈለሰፋችሁ፡፡
>
> ባቲዮኒ፡- (ለወጥ ይላል) ይህ አነጋገር ካፍ እልፊት የሚቆጠር ነው፡፡ ከሚፈቀደው አልፈው አይሂዱ ልብ ያርጉ፡፡
>
> (መንግስቱ፣ 1975a፣ገጽ 47)

ሽማግሌው በዚህ ንግግራቸው በምዕራብ-ምስራቅ ፍረጃ (Orientalism) ላይ እየተሳለቁ የማፍረስ *ሥራ* እያከናወኑ ነው፡፡ ጣልያን ሰለጠንሁ ብላ የሰራችው ህዝብን የሚጠቅም ሳይሆን የሚያወድም የመርዝ ጭስ ነው በማለት “እንዲህም ብሎ ስልጣኔ የለ" የሚል መልዕክት ሳይፈሩ ለባቲዮኒ እየነገሩት ነው፡፡ የአውሮፓ ማዕከላዊነት ዋና ማራመጃ የሆነው የምዕራብ ምስራቅ ፍረጃ (Orientalism) ማፍረሻ ሃሳብን ለማፍረስ ከሽማግሌው በላይ የተ*ጋ* የለም፤

> ሽማግሌ፡- አዬ የአውሮጳ ስልጣኔ አዬ ጥበብ፤ አዬ መልአክነን ያሉት ፊታቸውን በመስታወት ቢያዩት ይረዱት ነበር፡፡ ይህን ሁሉ መድፍ እና መትረየስ ታንክ እና አውሮፕላን የሰሩ፤ በባውዛ መብራት አየሩን የሚዳስሱ የሚደባብሱ ጠቢባን፣ እውነታኛዋን ገጻቸውን የምታሳየውን መስታወት ያችን ብቻ መስራት ተሳናቸው፡፡ መስታውቲቷን ቢያገኟትማ ሰልጥነናል ብለው ሊያሰለጥኑ ለመጡት ፍጹማን ፍጹም አረመኔነታቸው ወለል ብሎ በጉልህ በተከሰተላቸው ነበር፡፡
>
> (መንግስቱ፣1975a፣ገጽ 65)

እዚህ ላይ ነገር ተለወጠ፣ ቦታ ተቀያየረ፡፡ ምዕራብ አውሮፓ በምስራቁ የዓለም ክፍል ቦታ ተመደበ፡፡ ሽማግሌው ለአውሮፓ ማዕከላዊነት (Eurocentirism) ማራመጃ ለሆነው የምዕራብ ምስራቅ ፍረጃን (Orientalism) ትርክት ማፍረሻ ሃሳብ የሚሰነዝሩ ናቸው፡፡ በዚህ ትርክት ምዕራብ አውሮፓ ለራሳቸው የሰጡትን ፍረጃ የሚያሟሉ ቢሆኑ ኖሮማ የሰለጡኑ፣ ያወቁ፣ የመጠቁ የዘመኑ ቢሆኑ ኖሮማ አረመኔ ባልሆኑ ነበር እያሉ ይሞግታሉ፡፡ የእነሱ ስልጣኔ የሰው ልጆችን በመርዝ ጢስ መጨፍጨፍን፣ በአውሮፕላን ማርገፍን ብቻ የተካነ ነው የሚል አሽሙር በመንገር የምዕራብ-ምስራቅ ፍረጃን ያፈርሱታል፡፡ ምዕራቡ ለራሱ የሰጠው ግምት እና ሥዕል ፍጹም የተሳሳተ ነው እያሉን ነው፡፡ የምስራቁን ዓለም አረመኔ እና ጨካኝ ብለው ቢፈርጁትም ይህ ግን የሚገባቸው ለምዕራብ አውሮፓ ቅኝ ገዥዎች እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ሽማግሌው ይህን ሃሳባቸውን ይበልጥ እያጠናከሩ ቅኝ ገዥዎች ወይም ምዕራብ አውሮፓዊነት ማለት ከግብረ ገብነትና ከሰብዓዊነት የራቁ ለሰው ልጆች ክብር የሌላቸው መሆናቸውን ይነግሩናል፤

> ሽማግሌ፡- ዋሆዬ! ዋ አውሮጳ! ምንኛ እናደንቅሽ ነበር! ምንኛ እንቀናብሽ ነበር አዬ!ዋ ዝናሽ ማማሩ ስምሽ መጣፈጡ፣ ብርሃንሽ መድመቁ፣ መሞቁ ማንጸባረቁ፣ ያሁሉ የት

> አለ ዛሬ? የት ደረሰ? ምን በላው? የሮማ ብርሃን ልዩ አይነት ጨለማ ሆኖ ተገኘ፤ በእሳተ ገሞራ ጠብሰሽ ለመስዋትነት ያቀረብሽለት ተወው፡፡
>
> (መንግስቱ፣ 1975a፣ገጽ 65)

በምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ (Orientalism) ትርክት ምዕራብ አውሮፓ የስልጣኔ ብርሃናቸው አንጸባራቂ፣ የስልጣኔ ብርሃናቸው የሞቀ የደመቀ የሚለው የተሳሳተ ነው፤ የቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓ ወኪል የሆነችው ፋሽስቷ ጣልያን ድርጊትም የዚሁ ማሳያ እንደሚሆን ነግረውናል፡፡ በጭካኔ የተጨፈጨፈው የሰው ስጋ ከብዛቱ የተነሳ ጅብ እንኳ ጠግቦት አሽትቶ መተውን ስንመለከት የጭካኔውን ጥግ እንገነዘባለን፡፡ እናም ምዕራብ አውሮፓ ለራሳቸው ከሰጡት ትርክት በተቃራኒው የቆሙ ፍጹም የሰብዓዊነት ሽታ የሌላቸው፣ ጨካኞች፣ አረመኔዎች መሆናቸውን ሽማግሌው እየነገሩን ነው፡፡ ሰለጠንን ይላሉ እንጅ አልሰለጠኑም፤ ሩህሩህ ነን ይላሉ እንጂ ጨካኞች ናቸው፤ በእውቀት የበለጸግን እና ስልጡኖች ነን ይላሉ እንጅ ኋላቀሮች፣ አላዋቂዎች ናቸው፡፡ የሚል አንድምታ ያለው መልዕክት ሽማግሌው እያስተላለፉ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

ሆኖም በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* የቅኝ ገዥነትና ተገዥነት ትርክት እየተሸረሸረ እየተገለበጠ ሲሄድ እናስተውላለን፡፡ ኬንያዊው Ngugi wa Thiong'o የአዕምሮ ነጻነት ትግል (Decolonizing the mind) እንዳለው በሽማግሌው ካሴ፣ ውሂብ እና መሰል የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ዳግም ነጻነት ሲያመራ ይታያል፡፡ የቅኝ ግዛት ሥነ ልቦናም ተፍቆ እንዲወጣ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይስተዋላል፡፡ የኢትዮጵያውያንን ጥርስ ሲያራግፍ የነበረው ፋሽስቱ ሲኛር ፖጆ በውሂብ እግር ስር ወድቋል፤ ኢትዮጵያዊውን መጣፍ ገላጩን ጠንቋይ ውሂብን ለመለማመጥ ተገዷል፤

> ውሂብ፡- ይህን ወደል ገንዘቡን ደህና አድርገህ ቆንድድልኝ፡፡ ካሳዬ ነው፤ ጥርሴን በቡጢ ላረገፈው፡፡ …ወዲያ ጉዳዩን ተናግሮ ይሂድ ያስጠይፈኛል፡፡
>
> ፖጆ፡- ሁሉ በዚ [በዚህ] በዋራካት [በወረቀት] አላ [አለ] ኤኰ [እኰ] -ኢን አማሪኰ
>
> ውሂብ፡- አንብበው
>
> ካሴ፡- (ያነባል) ለተከበሩ ጌታዬ ጌታው አምበሶ፡፡ እኔ ካርሎ ፓጆ የተባልኩት ዝቅተኛ አገልጋይዎ ከዚህ በታች የሚቀጥለውን ለጌታዬ ሳመለከት ልቤን ቀን እና ሌሊት የሚያስጨንቀኝ ከባድ ጉዳይ መፍትሔውን እንደሚያገኙልኝ እተማመናለሁ ስል እጫማዎ ወድቄ እማጠንዎታለሁ፡፡ ክቡር ጌታዬ ሆይ አስር አስር ጊዜ እጅ እነሳለሁ፤ በጣልያን አገር በሲቺሊያ ደሴት የምትገኘውን ባለቤቴን በጠና አሚታል ብለው ጻፉልኝ፡፡ ሐኪም ሁሉ ሞከራ ሁሉም አቃታቸው፤ ምን ማድረግ ይሻለኛል? ነፍሴን ጨነቃት መፍትሔውን ቢያገኙልኝ ለዘልአለም አገልጋይ ባለውለታዎ እሆናለሁ! ይላል ባርያዎ፣ ካርሎ ፓጆ፡፡
>
> ውሂብ፡- የጻፈለት ሰው ቀልደኛ ነው! ጌታየን ባሪያዬ አድርጎታል (ያሰላስላል) በሚስትህ ያደረባት ሰባት ጋኔን ነው በለው፡፡ መድኃኒቱ ወፍራም ዶለዝ የሆነ ነጭ የፍየል ሙክት በሰላ ጎራዴ አርዶ ደሙን ለሴትዮዋ ማጠጣት ነው፡፡ [አፅንኦት የእኔ]
>
> (መንግስቱ፣1975a፣ገጽ 88)

የውሂብን ጥርስ ያረገፈው ካርሎ ፓጆ የውሂብ አገልጋይ ባርያ ለመሆን ወስኗል፡፡ ባሪያው አድርጎ ሲያንገላታው የነበረው የጣልያኑ ወኪል ካርሎ ፓጆ ለውሂብ ባርያ ሊሆነው ወስኗል፡፡ ውሂብ እና ካሴም ይህ ቅኝ ገዥ በሃገሪቱ ህዝብ ላይ ያሳደረውን የሥነልቦና መቃወስ ፍቆ

ለማስወጣት በካርሎ ፓጆ ላይ እየተሳለቁበት እናያለን፡፡ በመሆኑም በድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ አንጻር ካየነው ይህ ተውኔት በታሪኩ ማገባደጃ ላይ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን (Eurocentirism) አስተሳሰብ ሲያፈርስ፣ የድልድል (የገዥ-ተገዥ) ቦታ ሲያቀያይር፤ የምዕራብ ምስራቅ ፍረጃን (Orientalism) ሲፈረካከስ ይታያል፡፡ የኋላ ኋላም በንግርት መልክ ሲሰራጭ የነበረው "ጣልያን ቢገዛም ከአምስት ዓመት አያልፍም፤ በጀግኖች የኢትዮጵያ አርበኞች ተነቅሎ ይወጣል፤ ኢትዮጵያም ዳግም ነጻነቷን በእጇ ታስገባለች" የሚል መልዕክት ያስተላልፍልናል፡፡

## 3. የገዥ-ተገዥ ድልድል (Hegemony)

የገዥ-ተገዥ ድልድል ቅኝ ገዥዎቹ ምዕራብ አውሮፓ በአቅም፣ በዕውቀትም፣ በስልጣኔም፣ ለመግዛት ነው የተፈጠረው፤ አፍሪካን ጨምሮ ምሥራቁ የዓለም ክፍል ደግሞ ለመገዛት የተደለደለ ነው የሚል ትርክት የሚነዛ ነው። ይህም አንዱ የአውሮፓ ማዕከላዊነት ማራመጃ ስልት ሆኖ ቅኘ ተገዝዎቹ ፀጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ ማድረጊያ እንደሆነ እንረዳለን። የቅኝ ገዥዎች ምዕራብ አውሮፓ ወኪሎች ጣልያኖች ይህንን አስተሳሰብም በተላያየ መልኩ ከመስበክ አልተቆጠቡም፡፡ ቀጥሎ ያለው የባቲዮኒ ንግግርም የሚያሳዬን ይህንኑ ነው፤

> ባቲዮኒ፡- አወን አወን እግዜር ቸር ነው፡፡ ከባርነት ዘመን በጦር ስለት መንጥቆ እንዲያወጣችሁ የሮማን ብርሃን ላከላችሁ፡፡….ዛሬ ባርነት ጌትነት የለም፡፡ ያለው ገዥነት እና ተገዥነት ብቻ ነው፡፡ *ይህ አዲሱ የሰው በላይ አምላክ መሰል ሰው ገዥነት በዘሩ በደሙ ያለ ሲሆን መላውን ዓለም ረግጦ እንዲገዛ እንዲነዳ በታሪክ የታደለ ነው፡* ፡ እንግሊዞች “ሱፐር ማን” ይሉታል፡፡ ሌላው ተራው ዝቅተኛው ዘር በዚች መሬት በህይወት ቆሞ እንዲሄድ ከታሪክ የሚፈቀድለት ላምላክ መሰሉ የሰው በላይ ሰው ጠቃሚ አገልግሎት በመስጠቱ መጠን ብቻ ነው፡፡ አዲሱ የሰው በላይ ሰው መላው ዓለም የመሬቱን የሰማያቱን ሊያናውጥ የተነሳ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስካሁን ታይቶ እማይታወቅ አዲስ የተፈጥሮ ኃይል ነው፡፡ *አምላክ የሚባል ነገር ካለ አምላክ ማለት ይህ አዲሱ የሰው በላይ ሰው እሱ ራሱ ነው፡፡* [*አፅንኦት የእኔ*]
>
> (መንግስቱ፣1975a፣ገጽ 73)

ይህ የባቲዮኒ ንግግር የአውሮፓ ማዕከላዊነት ጥግ፤ ሁሉም ነገር ከአውሮፓ ይነሳል፤ ምዕራብ አውሮፓ ለገዥነት የተፈጠረ፣ ይህንንም ለማድረግ የሚያስችለው የደም እና ዘር ጥራት የተሰጠው ነው በማለት እያጠመቀ ነው፡፡ የሌላው ዓለም ሰው በደም እና በዘር የገዥነት መደብ ስላልተሰጠው ዕጣ ፈንታው መገዛት ብቻ ነው በማለት የገዥ ተገዥ ትርክትን (Hegemony) ይረጫል፡፡ ህዝቡ ማመጽን እንዲያቆም ትግሉን እንዳይቀላቀል ኢትዮጵያውያን የነጻነት አርበኞች የሚያደርጉት ትግልም ከንቱ ልፋትና ዋጋ የሚያስከፍላቸው መሆኑን አውቀው በደሙ እና በዘሩ የተገዥነት መደብ ለተሰጠው ለጣልያኑ ገናና ዱቼ ሞሶሊኒና ቪክቶር ቁሳር አማኑኤል መገዛት ይገባቸዋል፡፡ ይህን ሃሳብ በማራመድም የነጻነት ትግሉን የማቀዛቀዝ ተልዕኮ-ኮሎኒያሊስቱን ይፈጽማል፡፡ ይህ “አዲሱ የሰው በላይ አምላክ መሰል ሰው”ተብሎ በባቲዮኒ የተገለጸው ገናናው ዱቼ ሞሶሎኒ ወይም ደግሞ ቪክቶር ቁሳር አማኑኤል በደም እና በዘር ዓለምን የመግዛት ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ የሚያፈነግጠውን ረግጦ እስከመግዛት ድረስ ከልካይ የለውም፡፡ ሌላው ተራው ዝቅተኛው ዘር ብሎ በኢትዮጵያውያን ወኪልነት የተገለጠው የምስራቅ የዓለም ክፍል ህዝብ ደግሞ "ተረግጦ፣ እንደ በግ እየተነዳ ሊገዛ ግድ ነው፤ ማንገራገሩም ማመጹም ከንቱ ድካም በመሆኑ አሜን ብሎ መገዛት አለበት" በማለት የገዥ-ተገዥ የመደብ ድልደላን አምኖ እንዲቀበል (Hegemony) የሚያደርግ ነው፡፡

ባቲዮኒ ይህንን ሃሳብ ይበልጥ ሲያጠናክረው ከሮማ ቄሳር መንግስት በተፈጥሮ ከደሙ ከዘሩ የተሰጠው ስልጣን ዘላለማዊ እንደሚሆን ይሰብካል፡፡ እናም የአርበኞች ሆነ የውስጥ አርበኞች ትግል ከንቱ ድካም እንደሆነ ይገልጻል፤

> ባቲዮኒ፡- (በዲስኩር አነጋገር) ገናናው የጣልያን መንግስት የሚያሳድገው ለህዝብ እውነቱን የሚሰብኩትን ብቻ ነው፡፡ ምንድን ነው እውነቱ? ዳግማዊው የሮማ የቄሳር መንግስት ላለም ዘላለም መኖሩ ነው እውነቱ፡፡ ያበዱ የሽፍታ አለቆች አርበኞች ከሚባለው የወንበዴ ሰራዊት ጋ፤ የነሱ ድካም ሁሉ የህልም ሩጫ መሆኑ ነው እውነቱ፡ ፡
>
> (መንግስቱ፣1975a፣ገጽ 77)

ለእናት ሃገራቸው ነጻነት የሚፋለሙት አርበኞች የወንበዴ ሰራዊት ተብለው በጣልያን ተፈርጀዋል፡፡ እናት ሃገራቸውን ከባርነት ለማላቀቅ የሚዋደቁ ኢትዮጵያውያን ያበዱ ሽፍቶች ተብለው ተፈርጀዋል፡፡ እናም የሮማ ብርሃ የቪክቶር ቄሳር አማኑኤል መንግስት ዘላለማዊ ስለሆነ በከንቱ ደማቸውን ማፍሰስ፣ አጥንታቸውን መከስከስ እንደሌለባቸው ስብከቱን እየለቀቀው ነው፡፡ የሚሻለውም ለጣልያን ወደው ቢገቡ እና እጅ ቢሰጡ እንደሆነ በመንገር የነጻነት ትግል ስሜትን ለመቅበር እየሞከረ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ ባሻገር በአውሮፓ ማዕከላዊነት (Eurocentirism) አስተሳሰብ መነሻ በማድረግ የምዕራብ-ምስራቅ ፍረጃ (Orientalism) ምዕራቡን ገናና፣ ጀግኖች፣ በቴክኖሎጅ የመጠቀ ….፤ ምስራቁ ደግሞ ያበዱ፣ ሽፍቶች፤ የወንበዴ ሰራዊት ብሎ በመፈረጅ ጽንሰ ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከረ ነው፡፡

በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ተውኔት ውስጥ ሽማግሌው በአብዛኛው ለነፃነት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጡ ሆነው የተሣሉ ቢሆንም አልፎ አልፎ ደግሞ የጣልያን ብዝበዛና ግፍ እጅግ የሚያሥፈራና የሀገሬውን ሕዝብ እየጨረሰው በመሆኑ ከዚህ ካልባሰስ ይህንኑ አገዛዝ ለመቀበል ዝግጁ እንደሆኑ የሚጠቁም ንግግር ሲያደርጉ ይስተዋላል፤ ሕዝቡ ከሚያልቅ ባርነቱን የመምረጥ አካሄድ ነው (Hegemony)፤

> ሰውየው፡- እንደምን ዋሉ
>
> ሽማግሌው ፡- (በርጋታ) ዕድሜ ለግዜሀር የባሰ አያምጣ፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 25)

"ዕድሜ ለግዜሀር የባሰ አያምጣ" የሚለው ንግግራቸው ለነፃነት የሚደረግን ትግል የማቀዝቀዝ ኃይል እንዳለው ይሠማኛል፡፡ ከዚህ ካልባሰ ይህንኑ አገዛዝና የጭቆና ቀምበር ለመሸከም ሳይወዱ በግዳቸው ፈቃድ መሥጠታቸውን እንገነዘባለን (Hegemony)፡፡ እዚህ ላይ ቆራጡ ሽማግሌ ጽናታቸው ሊሰበርባቸው እያሥቸገራቸው እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከባርነት ሞት እፎይታ መሆኑን ሲገልጹ የሚታዩ ቢሆንም በዚህ ንግግራቸው ግን ሳይታወቃቸው በሚመስል መልኩ፣ የጣልያን ዘግናኝ ግፍና ጭካኔ ከዚህ እንዳይብስ እንጅ አሁንስ መገዛታችን የሚሻል መሆኑን ለመግለጽ ነው፤ "የባሰ አያምጣ" ማለታቸው፡፡

የባሰ አያምጣ አሜን ብሎ መቀበልን ማረጋገጥ ነው፡፡ ያለው እንዳለ ይቀጥል ለምን እናልቃለን ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ሽማግሌው ተጨንቀዋል፤ አብዛኛው ውስጣዊ ጥንካሬያቸው ነፃነትን ከማጣት ሞት እፎይታ መሆኑን በተጋጋሚ (በመደጋገም) የሚገልፁት ጥንካሬያቸው ነው፡፡

በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ጣልያኖችን ገዥወች ናቸው ብሎ የገዥና ተገዥ ትርክትን (Hegemony) አምኖ የመቀበል አዝማሚያ ያላቸውን ሀሳቦች የሚያራምዱ ባለታሪኰችም አሉ፡፡ እየተረገጡ፣ እየተቀጠቀጡ በልቶ ብቻ ለማደር የሚለማመኑ ባለታሪኰች አሉ፤ እንደገብረየስ ያሉት፤

> ገብረየስ፡- ጮኞ ቡጢ ነው፡፡ ዘሎ አገጬን ነው የሚለው፡፡ መንገጭሌውን ያወልቅለታል፡፡ እባክዎ አያ ውሂብን ይምከሩልኝ፡፡ በሲኞር ፖጆ አያያዝ አንዲት ጥርስ አትተርፈውም፣ ሁሉንም ያራግፍለታል፡፡ የሱ ጦስ ለኔም ተረፈ፡፡ አሞኛል ብሎ ከሥራ ይቀራል፡፡ ነጩ እኔን አምጣው ውለደው ነው፤ ከየት ላምጣ?
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 26)

የኢትዮጵያውያንን ክብር እንደፈለገው ማድረግ ሥልጣኑ የተሰጠው ለጣልያናዊው ሲኞር ፖጆ ይመስላል፡፡ ሲፈልግ ጥርስ ያረግፋል፤ ማንም ጠያቂ የለበትም፡፡ በገብረየስ ንግግር ይህንን ማናለብኝነትና ግፈኝነት አሜን ብሎ ከመቀበል ውጭ ምንም አማራጭ የሌለ መሆኑን እያሳየን ነው፡፡ በልቶ ለማደር የግድ ሲኞር ፖጆን ማስደሰት አለበት፡፡ ለሲኞር ፖጆ ማጐብደድ፤ መልመጥመጥና መለማመጥ ይጠበቅበታል፤ ካልሆነ ጥርሱ ይረግፍለታል፡፡ የፈለጋቸውን ለማድረግ፣ የፈለጋቸውን ለመፈፀም የተፈቀደላቸው እነሱ የቅኝ ገዥው ምዕራብ አውሮፓ ወኪሎች ጣልያኖች ሥለሆኑ የገዥና የተገዥ ድልድልን አምኖ መቀበሉን ያሳየናል (Hegemony)፡፡

ሽማግሌው የምዕራብ-ምሥራቅ ፍረጃ አስተሳሰብን ከማፍረስ መለስ ሲሉም የነፃነት ትግል የሚያፋፍሙ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የሀገሬው ሕዝብ ለጣልያን ቅኝ ግዛት ባርነት እጁን እንዳይሰጥ በከፍተኛ ወኔ እንዲታገል ሲያነሳሱ እንመለከታቸዋለን፡፡ ከባርነት ሺ ጊዜ ሞት ይሻላል የሚል የማይሰበር አቋም የያዙ ናቸው፡፡ ባርነትን ከመቀበል ሞት ረፍት እና "እፎይ" ማለት እንደሆነ ጽኑ አቋማቸው እንደሆነ ይገልፃሉ፤

> ሽማግሌ፡- ይህን ያህልም ልቤን የሰወረኝ አይምሰልህ። አንዳንደዬ ቀልቤን ይወስደዋል፡፡ ሲወስደው ሕሊናዬ እረፍት ያገኛል፡፡ ላንድ አፍታም ቢሆን ከዚህ ዓለም ይለየኝና አርፋለሁ፡፡ ሰው አብዷል ቢለኝ የኔን እብደት እኔ የምጠላው አይምሰልህ፡፡ እረፍት ነው፤ እፎይ ማለት ነው"፡፡
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 23)

ይህ ንግግራቸው በቅኝ ተገዥዎች በኩል ነጮችና በተለይ ደግሞ ምዕራብ አውሮፓ ለመግዛት ዓለሙን ለማሠልጠን ነው የተፈጠሩት፤ ከዚያ ውጭ ያለው ዓለም ግን ለዚህ አልደረሰም፣ አልበቃም፤ እናም መገዛት ይሻለናል፤ በማናውቀው ጉዳይ ራሳችንን በራሳችን ለማስተዳደር ሥንሞክር ብዙ ነገር ከምናበላሽ በቁርጡ  የቅኝ ገዥዎች አገዛዝ ይሻለናል፤" የሚለውን (Hegemony) አስተሳሰብ የሚሰባብር ነው፡፡ ሽማግሌው "በባርነት በእነሱ ከመገዛት፣ ነፃነትን ከማጣት መሞት እፎይታ መሆኑን በመግለጽ የምዕራብ አውሮፓን ገዥነት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ የምስራቁ ዓለም ተገዥነት ድልደላ በፍፁም የማያምኑበትና የማይቀበሉት መሆናቸውን እየነገሩን ነው፡፡

ይህ አስተሳሰባቸውም በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ሠርፆ እንዲገባ (ለምሳሌ በውስጥ አርበኛው ውሂብና ካሴ) በተለያየ መንገድ ከመግለጽ አይቆጠቡም፡፡ ነፃነትን ከማጣትና በባርነት ውስጥ ከመኖር እብደታቸውን፣ የአእምሯቸውን መቃወስ መምረጣቸውን ስናስተውል የሀገራቸውን ነፃነት ምን ያህል አጥብቀው እንደሚሹት የምንረዳበት ጥቅስ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው ለአውሮፓ ማዕከላዊነት አልገዛም ማለታቸውን ያሳየናል፤ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን ከመቀበል ሞት እፎይታ እንደሆነ የውስጥ ስሜታቸውን የሚገልፁበት ነው።

"*እረፍት ነው፤ እፎይ ማለት ነው*" [*አፅንኦት የእኔ*] በሚሉት የሽማግሌው ንግግር ወስጥ ያሠመርሁባቸው ሁለቱ ቃላት የያዙት መልዕክት በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፡፡ እረፍት ነው፤ የሚለው "አይ እከሌ ያን ያህል ዓመት በህመም ሲሰቃይ ከመከረሙ ሞቱ ረፍት ነው"

የሚለውን ያሳይልናል፤ ነፃነትን ከማጣት በላይ ለሽማግሌው ከፉ ህመም የለባቸውም፡፡ እናም ሞታቸው ረፍታቸው እንደሆነ በመግለጽ ቆራጥነታቸውን እየነገሩን ለአውሮፓ ማዕከላዊነት አሻፈረኝ ማለታቸውን እንገነዘባለን፡፡

"እፎይ ማለት ነው" የሚለውም የዋዛ አይደለም፡፡ ለነፃነታቸው ሲሉ መሞት ምን ያህል ደስታን እንደሚሰጣቸው ሲነግሩን ነው እፎይ ማለታቸው፡፡ "እፎይ" አንድን ነገር በደስታ መቀበልን፤ ተገላገልሁት ማለትን ሊገልጽ የሚችል ጥልቅ ስሜትን የያዘ በመሆኑ ሽማግሌው በባርነት ከመማቀቅ፣ ነፃነትን ለማስመለስ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን፤ በዚህ ውሳኔያቸው የሚደርስባቸው የሕይወት መነጠቅ ለአሳቸው "እፎይ" የሚያሰኝ ደስታ እንጂ ሐዘን አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

## *ቋንቋ፡-ድምፅ አልባው ጠመንጃ*

በድህረ ቅኝ ግዛት ሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ ሌላው ጎልቶ የሚመጣው ጭብጥ ቋንቋ ነው። Ngugi (1994:3) ይህንን በቋንቋ በኩል የሚደረገውን የቅኝ ገዥዎች ጫናም፣ “ባህል አውዳሚው ቦምብ” ሲል ይገልፀዋል። ቅኝ ገዥዎች በጦር ካደረጉት ወረራ በበለጠ ሁኔታ የአውሮፓ ማዕከላዊነት አስተሳሰብንና ትርክትን ይዞ የምዕራብ አውሮፓን ባህል፣ ወግ፣ ማንነት፣ ትውፊት፣ ለቅኝ ተገዥ ሀገራት እንደሽቀጥ ያራገፉበት መሣሪያ ቋንቋ ነው።

ይህ በቅኝ ገዥዎች የሚደረገው የቋንቋ ብዝበዛና ጫናን ሁኔታ በመንግስቱ ለማ *ፀረ ኮሎኒያሊስት* ተውኔት ተንፀባርቋል። በ*ፀረ ኮሎኒያሊስት* በስፋት የቋንቋ ቅኝ ገዥነት የሚታይበትና ወደ ማህበረሰብ የመስፋፋት ደረጃ ሲያሳይ አስተውያለሁ። በተውኔቱ ውስጥ የቋንቋ ተፅዕኖና የበላይነትን ሊያሳዩልኝ የሚችሉ ቅንጭብ ሃሳቦችን እያቀረብሁ እንተነትናለን፤

> ገብረየስ፡- ፑኞ ቡጢ ነው፡፡ ዘሎ አገጩን ነው የሚለው፡፡
>
> (*መንግሥቱ*፣ 1975a፣ገጽ 26)
>
> ሽማግሌ፡- ስነግራችሁ! ማን አለ ያልተለወጠ? ማን እንዳኖሩት ተገኘ? የራበው ለሆዱ ማተቡን በጠሰ። *ፌርማቶሪው* ሰላዩ በዛ፤ እርስ በእርስ መጠራጠር ሆነ፤ አንዱ አንዱን አያምነውም። ሴቲቱ ጣት ላይ ቀለበት አየ አሉ ባንዳው። አልወልቅም ቢለው በሳንጃ ጣቷን ጎረደው። [*አፅንኦት የእኔ*]
>
> (*መንግስቱ*፣1975a፣ገጽ19)

ከላይ በጥቅሶቹ ውስጥ የተስተናገዱ ቋንቋ ገላጮች፣ *ፑኞ፣ ባንዳ፣ ፌርማቶሪው፣* የሚሉት ቃላት እና ዓረፍተ ነገሮች በወቅቱ ቅኝ ገዝዎች በከፍተኛ ፍጥነት ቋንቋቸውን እየጫኑ እያስፋፉት እንደነበር የምንረዳባቸው ናቸው። የአማርኛው ቡጢ እያለ ገብረየስ ቀድሞ አፉ ላይ የመጣው *ፑኞ* የሚለው የጣልያን ቃል ነው። ገብረየስ ይህንን ቃል ወዶና ፈቅዶ የለመደው አይመስለኝም። ጫና አለበት፣ በሕይወት የመኖር ጫና፣ በልቶ የማደር ፈተና።

በ*ፀረ ኮሎኒያሊስት* ውስጥ የምናገኘው ገብረየስ ለጣልያን በጉልበት ሠራተኝነት የሚያገለግል፣ ከፍተኛ የሆነ የጉልበት ብዝበዛ የሚፈፀምበት፣ በአሰሪው የጣልያን ተወካይ ፋሽስቱ ሲኞር ፖጆ ሰበብ እየተፈለገለት አገጩ በቡጢና እርግጫ የሚወልቅለት የቅኝ ግዛት ሰለባ የሆነ ባተሌ ነው። ከጉልበት *ሥራው* ትንሽ በዘገየ ቁጥር ከፖጆ ድብደባ ባለፈ ደሞዙ የሚቆረጥበትና በልቶ ለመኖር ችግር ውስጥ የወደቀ መሆኑን እንረዳለን። ከዚህ ሁኔታው በመነሳትም ገብረየስ የአሳዳሪውን የሲኞር *ፖጆን* ጣልያንኛ ቃል *ፑኞን* መጠቀም ግዴታ ሆኖበታል ማለት እችላለን።

የወራሪዎቹ ጣልያን ቋንቋ በአጭር ጊዜ ወደ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለመግባቱ *ፀረ ኮሎኒያሊስት* ውስጥ የምናገኛቸው ሽማግሌው ማስረጃ ይሆኑኛል። ሽማግሌው ምንም ያህል

የጣልያንን ቅኝ ግዛት የሚቃወሙና አምርረው የሚተቹ ቢሆኑም የጠሉትን መውረሳቸው ግን አልቀረላቸውም። *ሰላይ* በማለት ምትክ *ፌርማቶሪን* መርጠው ተጠቅመዋል። ማናልባትም ሰላይነት በተለይ ደግሞ የሀገሩን ነፃነት ለገፈፈው ጣልያን በሰላይነት *መሥራት* አስነዋሪ ተግባር ነው። በመሆኑም ይህንን አስነዋሪ ድርጊት ኢትዮጵያውያን አማርኛ ቃሉ የወከለውን ትርጉምና ምስል ስለሚጠሉት ይህን አስነዋሪነቱን ለመሸፋፈን ጣልያንኛውን *ፌርማቶሪ* ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ጣልያንና ባንዳዎቹ በሰፊው ሰርተዋል የሚል አንድምታ ማግኘት ይቻላል። ከዚህ በመነሳትም ሽማግሌው የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወኪል ናቸው ብለን ብናስብ ጣልያንኛ ወደታችኛው ማህበረሰብ እየሰረፀ መሆኑን ይጠቁሙናል።

ይህን የማህበረሰብ ገፅታ በሌላ መልክም እናገኘዋለን። *"ስለኰማንዶ- ስለኰማንዳቶሪ - ስለኰማንዳ ባንዳ - ስለ ባንዳ ባንዳ ኰማንዳ"* [*አፅንኦት የእኔ*] (መንግስቱ፣1975a፤46)። እነዚህ በ*ፀረ ኮሎኒያሊስት* ውስጥ የምናገኛቸው የእሳቱ የልመና ቃላት ናቸው። ፈጣሪውን በሀገሩ ቋንቋ በአማርኛ ጠርቶ ከመለመን ይልቅ የዕለት ሆዱን የሚሞሉለት ጣልያኖችንና ባንዳዎችን በጣልያንኛ ቋንቋ እየጠራ መለመንን መርጧል። በመሆኑም አብልቶ በማሳደር ሰበብ የአውሮፓ ማዕከላዊነት ወኪል ሆና በምሥራቅ አፍሪካ በምትንቀሳቀሰው በጣልያንኛ ቋንቋ መለመን ተገዷል። ይህ እንግዲህ የቋንቋ ጫናው በምን ያህል ፍጥነት ወደ ማህበረሰቡ እንደተስፋፋ የሚያሳየን ነው። ከዚህ ባለፈ ጣልያን በነባሩ ቋንቋ ላይ ባሳደረችው ጫና በተውኔቱ ውስጥ እንደሚገለፀው ስለ ማርያም፣ ስለ ገብርኤል፣ ስለ ሚካኤል፣ ብሎ መለመንን አስከዷል። እንግዲህ በዚህ ቋንቋ በተላለፈው መልዕክት "አምላክ አከሉ የሰው የበላይ" ብለው የፈረጁት ገናናው ዱቼ ወይም ደግሞ ቪክቶር ቄሳር አማኑኤል ከፈጣሪ ይስተካከላል በማለት ለሃይማኖቱ ቀናኢ የሆነውን የኢትየጵያን ሕዝብ ህልውናውን እያናጉበት፣ እያፈረሱበት፣ እያወደሙበት ነው የሚል አንድምታ እንዳለው አስስባለን፤

> ሽማግሌ ፡- *ፖጆ ፖጆ ሲኞር ፖጆ* - የሚባለው ይህ ነው፡፡ በቡጢ ያወለቀው መንጋጋ ቁጥር የለውም፡፡ ያረገፈው የሀበሻ ጥርስ በእንቅብ ይሠፈራል፡፡ የእርግጫው ስሙ "*ካቻን ኩሎ*" ይባላል አሉኝ ልጆቹ፡፡ [*አፅንኦት የእኔ*]
>
> (መንግሥቱ፣1975a፣ገጽ 21)
>
> *የፋሽሽ[ስ]ት* ወታደሮች የሚዘምሩት የሰልፍ መዝሙር እየቀረበ እየጎላ ሲሄድ፣ የሰልፈኞቹ ኮቴ ቸብ - ቸብ - ቸብ ይላል መዝሙራቸው "*ሮማ ሪቤንዲካ ሊምፒሮ*" የሚለው ነው (ሮማ ብድራን መልሳ ጥንታዊ ግዛቷን እጅ ታደርጋለች ማለት ነው።) "*የናርኩ ኢጋሰሸ*' የተባለው *ትሬንታኳትሮ ካሚዮን* ያኮርፋል፣ አልፎም ያጓራል፡፡ [*አፅንኦት የእኔ*]
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 18)
>
> ፫ኛው ልጅ፡- እኔ እምፈራላቸው ትሬንታካትሮውን ካሚዮን ነው በካሚዮን ይድጣቸዋል።
>
> ፭ኛው ልጅ፡- የለም እኔ እምፈራው አንዱ ሬዚዴንሳ ሂዶ ለኮማንዳቶሬው እንዳይነግርባቸው ነው።
>
> (መንግሥቱ፣ 1975a፣ገጽ 20)

ከፍ ብሎ የተጠቀሱት "ካቻን ኩሎ"፣ "ሮማ ሪቤንዲካ ሊምፒሮ"፣ "የናርኩ ኢጋሰስ"፣ "ትሬንታኳትሮ ካሚዮን" የሚሉት በጣልያንኛ ቋንቋ የተገለፁ ንግግሮች ብዙ መልዕክቶችን የያዙ መሆናቸውን እንረዳለን። *ካቻንኩሎ* የጣልያን የብዝበዛ ማስፈፀሚያ እርግጫ ነው።

ፋሽስቱ ጣልያን የአውሮፓ ማዕከላዊነት የሰጠውን የበላይነት ተጠቅሞ ፈላጭ ቆራጭነቱን የሚገልፅለትን ካቻንኩሎን በሕዝቡ ውስጥ አስርጿል። *ካቻንኮሎ* "አስፈሪ ነኝ! ማንም አይነካኝም" ለማለት በጣልያንኛ ቋንቋ ያስተላለፈው ሀይልና ጉልበቱን አመላካች መልዕክት የያዘ አንድምታ አለው።

"ሮማ ሪቤንዲካ ሊምፒሮ"፣ የሚለው ሃሳብ ደግሞ በጣልያንኛ ቋንቋ ተሻግሮ የጣልያን ገናናነትና አይበገሬነት የተገለፀበት ነው። በአማርኛው ሮማ ብድሯን መለሰች በማለት "በጦር ሀይልም፣ በስልጣኔም፣ በዘመናዊነትም፣ በጥበብም፣ ኢትዮጵያ ልትወዳደራት አትችልም" የሚል ይዘት ያለው ሃሳብ ለማራመድ የተጠቀሙበት ነው የሚል ዕይታ አለኝ። የበላይነትን በአድዋ ጊዜ የደረሰባቸውን ሽንፈት አምነው ላለመቀበል 40 ዓመታት ሙሉ ተዘጋጅተውበት መጥተው የፈፀሙትን ግፍ ማካካሻ መሆኑን ያስተላለፉበት ቋንቋ ነው።

ሌላው እስከ አሁን ድረስ ለተሽከርካሪዎች ሌላ *ሥያሜ* ማውጣት የማይቻልበት እስኪመስለን ድረስ ያኔ በጣልያን ለተጫነው ማሳያ የሚሆነን፣ *ትሬንታኳትሮ ካሚዮን* የሚለው ነው። ከዚህ በመነሳት ጣልያኖች ራሳቸውን የሜካኒካል ምሕንድስና መነሻና መድረሻ፣ የተግባር ሙያ ልህቀት አብነቶች አድርገው የፈረጁበት መሆኑን ያሳየናል። ዛሬ ላይ በሀገራችን መኪና እና ሾፌር የሚሉትን ሥያሜዎች ጨምሮ ሌሎች የተሽከርካሪ ዕቃዎች ከጣልያንኛ ቋንቋ ውጭ በሀገረሰብ ቋንቋ መሰየም እስከ መቸገር ደረጃ የደረሰ የቅኝ ገዠዎቹ የቋንቋ የበላይነትና ሥርፀትን የምንረዳበት ቅንጭብ ሃሳብ እንደሆነ አናስባለን።

ከላይ በጠቃቀስኳቸ ማሳያዎች በመነሳት ጠልያኖች ጣልያንኛ ቋንቋንና በውሥጡ የተሸከማቸውን የአውሮፓ ባህል፣ ወግ፣ ማንነት፣ ትውፊት፣ በኢትዮጵያውያን ላይ በጉልበት ለመጫን ሲፈፅሙት ለነበረው ግፍ ቀጣዩ በሽማግሌውና በፖጆ መካከል የሚደረገው ልውውጥ ዐቢይ ማሳያ የሚሆኑ ናቸው፤

> *ፖጆ*፦ ኤይ! ሳሉታ! ---ሳላምታ! ፔርኬ ኖንሳ ሉታሬ?
>
> ሽማግሌ፦ እስከ *መቼ*፣ እስከመቼ ድረስ ቸል ትለኛለህ?
>
> *ፖጆ*፦ *ፖ*ርካ - ላሚዜሪያ!....ሳሉታ ኮዚ! ---ሳላምታ! አላ ሚነዬራ ፋሺስታ!
>
> ሣላምታ!
>
> ሽማግሌ፦ (ይባንናሉ) ምን አድርግ ነው?
>
> *ፖጆ*፦ (ያምባርቅባቸዋል) ሳሉታ! (ራሱ የፋሺስት ሰላምታ ሰጥቶ አሰጣጡን ያሳያቸዋል። ግራ ገብቷቸው እጃቸው ከግምባራቸው ይወርዳል። ሶልዳቶው ይብስበታል።...) ኩዌስቶ ኤ ኡን ሜዞ - ማቶ! ሴዪ ማቶ! ካፒሺ? ማቶ! ሉና ቲኮ! ---- ኢብድ ኖ አንታ!
>
> (*መንግሥቱ*፣ 1975a፣ገጽ 22)

ከዚህ የሁለቱ ሰዎች ንግግር፤ ሀይል እና ጉልበቱ በማን እጅ ላይ እንዳለ የምንረዳበት ነው። ሀይል፣ ጉልበቱ፣ ፈላጭ ቆራጭነቱ በእጃቸው ስለገባም አዛውንቱን በግድ በጣልያንኛ ሰላምታ ካልሰጡኝ ብሎ ቁም ስቅላቸውን ሲያሳያቸው መመልከታችን የቅኝ ገዥዎቹ ቋንቋን ጫና በደንብ ያሳየናል።

ከሁለተኛው የጣልያን ወረራ ጊዜ ጀምሮ ጣልያንኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ውስጥ እየያዘ የመጣው ሰፊ ቦታ ምን ያህል እንደነበር ተከታዩን ቅንጭብ ሃሳብ በማሳየት ይህንን ክፍል ልቋጨው። *ደረጃ አዳሪ፦ ለተንኮል ከሩቅ ሆኖ "ሲኞር ቆንጆ፣ ፓኔ!*

*መንጀሪያ!'' ብሎ ዳቦ ሲለምን ጊዜ ሶልዳቶዎቹ ሁሉ ''ሆዋ'' ብለው ሳቁ* [*አፅንኦት የእኔ*] (*መንግሥቱ*፣ 1975a፣*ገጽ* 35)፡፡

የዚህ ህፃን ንግግር አማርኛ ቋንቋ ወይም ሌላ የኢትየጵያ ቋንቋ ከሀገሬው አንደበት ውስጥ አፈትልከው እየወጡ፣ ለጣልያንኛ በጉልበት ቦታቸውን እያስረከቡ መሆኑን ነው። ልጁ ከንግግሩ ውስጥ ብዙ ጣልያንኛ ቃላትን መጠቀሙ ደግሞ የአውሮፓ የበላይነትን የሚያነግሰው የአውሮፓ ቋንቋ ሥር እየሰደደ፣ ሥር እየያዘ መሆኑን የምንገነዘብበት ይሆናል።

## ማጠቃለያ

በፀረ-ቅኝ ግዛት ንግግር ውስጥ በንድፈ ሃሳብ እና በተግባር መካከል ያለውን መስተጋብር ለማብራራት ባለው ፍቅር የተነሳ ይህ ጥናት  በፀረ ቅኝ ግዛት  ውስጥ የድህረ ቅኝ ግዛት ጭብጦችን በጥልቀት ወደ ትንተና ያስገባል። ጥናቱ ከትረካው የቅኝ ግዛት ሃይል ተለዋዋጭነት እና የነሱ ሌጋሲ ጎን ለጎን የሚያስተጋባ ጉልህ የንድፈ ሃሳባዊ መግለጫዎችን በማግኘቱ ስራውን በጥልቀት አይቷል። ይህ ጥንቃቄ የተሞላበት የግኝት ጉዞ  ራሱ እንዴት ከቅኝ ግዛት በኋላ ጽንሰ-ሀሳቦችን እንደሚያንጸባርቅ እና ከታሪክ እና ከማንነት ጋር ያለውን ቁርጠኝነት ለመረዳት ጠቃሚ መነፅርን ይሰጣል።

*ፀረ ኮሎኒያሊስት* የቅኝ ግዛት *ሥነ* ጽሑፍ ንድፈ ሀሳብ መገለጫ ጭብጦችን የሚንፀባረቅበት መሆኑን ተረድተናል፡፡ በ*ፀረ ኮሎኒያሊስት* ተውኔት ውስጥ ኢትዮጵያ በጦር ሀይል በቅኝ ግዛት *ሥር* አልዋለችም ቢባልም የእጅ አዙር የቅኝ ግዛት ተፅዕኖ ሰለባ መሆኗን አሳይቷል፡፡ ከተውኔቱ እንደምንረዳው በአድዋ ላይ የተደረገው ኢትዮጵያን ቅኝ የማድረግ ወረራ በፍፁም ተጋድሎ ስላልተሳካ ከ40 ዓመታት በኋላ ደግሞ ጣልያን ሁለተኛውን ወረራ አድርጋ በጦርነት አሸንፋ አምስት ዓመታት ሙሉ ብትቆይም በኢትዮጵያውያን አርበኞች ተጋድሎ ምክንያት ረፍት ማጣቷንና ቅኝ ገዥነቷን ማረጋገጥ አልቻለችም፡፡

ሆኖም ከሁለተኛው የጣልያን ወረራ ያልተሳካ ሙከራ በኋላ አውሮፓውያን ዋና ቅኝ የማስገዣ መንገድ አድርገው የተጠቀሙት ኢትዮጵያውያንን ወደ አውሮፓ ልኮ በማስተማር ሰበብ ማስኮብለልና የአውሮፓ ማዕከላዊነት አራማጆች እንዲሆኑ በማድረግ በኩል እንደተካሳላቸው በተውኔቱ ላይ ባደረግነው ምርመራ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ ከሁለተኛው የጣልያን ወረራ በኋላ እንደ ዋና ጉዳይ ሆኖ በሀገሪቱ ዜጐች ላይ የተስተዋለው የአውሮፓን ትምህርት የሥልጣኔ ምንጭ አድርጐ መቁጠርም በጉልህ መስተዋሉን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ግኝት በምዕራብ አውሮፓ በጦር በቅኝ መግዛት ያልተቻለ ብንሆንም የትምህርት ሥርዓት በማስረጽ፣ ባህልን፣ ማንነትን፣ ትውፊትን፣ ወግን እንደሸቀጥ በማራገፍ ለህሊና ቅኝ ተገዥነት የተዳረጉ ባለታሪኮችን በተውኔቱ በተቀረፁት ገፀባህሪያት ታሪክ ወኪልነት ማረጋገጥ  ችሏል፡፡

ከነዚህ በመነሳትም *ፀረ ኰሎኒያሊስት* ተውኔት የድህረ ቅኝ ግዛት የሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳብ መገለጫዎችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ችለናል። በ*ፀረ ኰሎኒያሊስት* ተውኔት ሽማግሌው፣ ውሂብና ካሴ የአውሮፓ ማዕከላዊነትን (Eurocentirism) ትርክት በማፍረስ በኩል ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አስተውያለሁ። የምዕራብ - ምሥራቅ ፍረጃን (Orientalism) በማፍረስና ቦታውን በማቀያየር በኩል የተጫወቱት ሚናም ከፍተኛ ነው።

# Declarations

**Conflict of interest**

The authors declare that there is no conflict of interst

**Funding**

The first author received financial support from Bahir Dar University

# ማጣቀሻዎች

## I. የአማረኛ ማጣቀሻወች

መንግሥቱ ለማ:: (1975) ። *የተውኔት ጉባኤ* :: አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

መንግሥቱ ለማ። (1975a)። ፀረ ኰሎኒያሊስት። *የተውኔት ጉባኤ* (ከገፅ 13-108)፨ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

መንግሥቱ ለማ። (1975b):: ባለካባና ባለዳባ:: *የተውኔት ጉባኤ* (ከገፅ 109-178)፨ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

## II. የእንግሊዘኛ ማጣቀሻዎች

Ashcroft, B., Griffiths, G. & Tiffin, H., (Eds.) (1995). *The post-colonial studies reader*. New York, Routledge.

Ashcroft, B., Griffiths, G., & Tiffin, H. (Eds.). (2004). *The empire writes back: Theory and practice in post- colonial literature* (2nd ed.). London: Routledge.

Bahru Zewde (2002). *A history of modern Ethiopia, 1855–1991* (2nd ed.). Oxford: James Currey; Athens: Ohio University Press.

Bertens, H. (2007). *Literary Theory: The Basics*. London & New York: Routledge.

Bhabha, H. K. (1990) (ed.). *Nation and Narration*. London & New York: Routledge.

Bhabha, H. K. (1994). *The location of culture*. London: Routledge.

Dobie, A. (2012). *Theory into Practice: An Introduction to literary criticism.* Wadsworth, USA: Cengage Learning.

Fanon, F. (1952) *Black skin, white masks* (trans. Charles Lam Markmann). London: MacGibbon and Kee.

Fanon, F. (1961). *The wretched of the earth* (trans. by C Farrington). London: MacGibbon.

Habib, M.A.R. (2005). *Modern literary criticism and theory: A history*. Blackwell Publishing: USA.

Harrison, K. (2003). *Post-colonialism: History, theory and work of fiction.* Cambridge, UK: Polity Press.

Mahlet Abraham (2006). Colonization, cultural conflict and identity crises [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Melakneh Mengistu. (2008). Post-colonialism and mainstream Anglophone African novel (ca.1970-2000): A Comparative approach [Unpublished doctoral dissertation]. Addis Ababa University.

Ngugi, W.(1994). *Decolonizing the mind: The politics of language in African literature*. Harare: Zimbabwe Publishing House, Ltd.

Regassa Kebede. (1980). Neo-colonialism and the third world: The case of the United States-Ethiopian Relations since 1940's [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Said, E. W. (1978). *Orientalism*. London: Routledge.

Spivak, G. (1988). *In other worlds: Essays in cultural politics.* London: Routledge.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today* (2nd ed.). New York: Routledge.